# የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ ።

## ከ፲፫ኛው ፡ እስከ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ።

ከዶክተር ፡ ጃ ፡ ቫንደርሊንደን ። *

### መግቢያ ፤

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ከ፲፫ኛው ፡ እስከ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ ስለሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ መግቢያ ፡ ነው ።

መግቢያ ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ አንባቢው ፡ ይህን ፡ አጭር ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ የተሟላና ፡ የተጠቃለለ ፡ መግለጫ ፡ የያዘ ፡ አድርጎ ፡ እንዳይገምተው ፡ ነው ። በመጽሐፉም ፡ የምንመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ በሳይንስ ፡ ረገድ፡ በደንብ ፡ መጠናት ፡ የተጀመረ ፡ በቅርቡ ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የሚቆጠር፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ለመሞከር ፡ ያቀድነው ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ የምናውቀውን ፡ በአጭሩ ፡ ለመግለጥና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የዚሁ ፡ ጥናት ፡ ዕድል ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ለመናገር ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ ወይም ፡ መገኛ ፡ ማናቸውም ፡ የተመዘገበ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ምንጮቹ ፡ ብዙዎቹ ፡ በጽሑፍ ፡ ተመዝግበው ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆኑ ፡ በቃልም ፡ የሚውሉ ፡ ; ሉ ። እነሱም ፡ ባጭሩ ፡ ሕጉ ፡ የሚገለጽባቸውና ፡ የሚታይባቸው ፡ ማናቸውም ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ደንበኞቹ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ለምሳሌ ፡ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ሕጎች ፡ ልማድ ፡ ፍርዶች ፡ የሕግ ፡ ሳይንስና ፡ የሕግ ፡ ሰነዶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ ከማይቆጠሩት ፡ ለምሳሌ ፡ ከታሪክ ፡ ከአገር ፡ [illegible] ፡ ጽሑፍ ፡ ከጋዜጦች ፡ ከድርሰቶችና ፡ ከሌሎችም ፡ ጭምር ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ የሚገኙ ፡ በጽሑፍ ፡ ተመዝግበው ፡ ወይም ፡ በቃል (በድምፅ)፡ ተመዝግበው ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ በቃል ፡ ንግግር ፡ መቅረጫ ፡ (በማግኔት ፡ ቴፕ ፡ ሬከርድ) ፡ የተመዘገቡ ፡ አሉ ።

አሁን ፡ ለተነሳንበት ፡ ዓላማ ፡ እንዲመች ፡ በማለት ፡ ለሕግ ፡ የምንሰጠው ፡ ትርጉም ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ አንድነትና ፡ እድገት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ሕዝብ ፡ ባወቃቸው ፡ ድርጅቶች ፡ አማካይነት ፡ በግዴታ ፡ የሚከበሩት ፡ እድራጎቶችና ፡ ኢንስቲቱሲዮኖች ፡ ነው ። ሕግ ፡ ሊባል ፡ የሚችለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለማጠቃለል ፡ እንዲመቸን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለሕግ ፡ የሰጠነው ፡ ትርጓሜ ፡ በጣም ፡ የሰፋ ፡ ነው ። ትርጉሙም ፡ ሕግ ፡ ሰው ፡ በማኅበር ፡ ከመኖሩ ፡ የተነሳ ፡ የሚገኝ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ሕግ ፡ ኢንስቲቱሲዮኖችንና ፡ እድራጎቶችን ፡ የሚጠቀልል ፡ መሆኑን ፡ ሕግ ፡ በኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በታወቁ ፡ ድርጅቶች ፡ አማካይነት ፡ እንዲከበር ፡ መደረጉን ፡ በመጨረሻም ፡ የሕግ ፡ ዓላማዎች ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ አንድነትና ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ እድገት ፡ መሆናቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

---

*ሑፕልያ ፡ አ ፡ ላዩኒቨርሲቲ ፡ ሊብር ፡ ደ ፡ ብሩሰልስ ፡ በጉብኝት ፡ መልክ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ለማስተማር ፡ የመጡ ።

ለአቶ ፡ አሰፋ ፡ ሊበን ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኘውን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በፈቃደኛነት ፡ ስለተረጐሙልን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብላቸዋለሁ ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የምናየው ፡ ጉዳይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ እናያለን ።[1]

የምናጠናውን ፡ ጉዳይ ፡ በዘመን ፡ ስንመለከተው ፡ በስምንት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ የያዘ ፡ ነው ። ፲፫ኛውን ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መነሻ ፡ እንዲሆን ፡ የመረጥነው ፡ ስለ ፡ አገሪቱ ፡ ሕግ ፡ ሁናቴ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ጠቃሚ ፡ የተመዘገቡ ፡ ጽሑፎች ፡ የሚገኙበት ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ሌሎች ፡ ዘመናት ፡ የተመዘገቡ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ፤ ሆኖም ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመትና ፡ በሚከተሉት ፡ ዘመናት ፡ ከተመዘገቡት ፡ ጋር ፡ አይወዳደሩም ። የጥናታችን ፡ መነሻ ፡ ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ መድረሻው ፡ ደግሞ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ አሁን ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ የዛሬውንም ፡ ሁናቴ ፡ ይመለከታል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጠቅላላ ፡ የዘመን ፡ ክፍል ፡ የተሰጠውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ በአራት ፡ ክፍል ፡ እንመድበዋለን ፤ ይኸውም ፡—

፩ ፤ ከ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ማለት ፡ የሰሎሞን ፡ ነገድ ፡ ነገሥታት (እንደገና) ፡ መንገሥ ፡ ከጀመሩበት ፡ አንስቶ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እስከ ፡ ነገሡበት ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፹፱ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ ያለውን ፡ ከምኒልክ ፡ በፊት ፡ ያለ ፡ ዘመን ፡ እንለዋለን ።

፪ ፤ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከነገሡበት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ እንደራሴ ፡ እስከ ፡ ሆኑበት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የምኒልክ ፡ ዘመን ፡ እንለዋለን ።

፫ ፤ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ እንደራሴ ፡ ከተባሉበት ፡ ጀምሮ ፡ (እ. ኤ. አ.) በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ.ም. እስከ ፡ ተጀመረው ፡ የኢትዮጵያና ፡ የጣሊያን ፡ ጠብ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ያለ ፡ ዘመን ፡ እንለዋለን ።

፬ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከተመለሱበት ፡ (እ. ኤ. አ.) ከ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ.ም. ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ያለውን ፡ ያለንበት ፡ ዘመን ፡ እንለዋለን ።

የነዚህ ፡ ዘመናት ፡ አመዳደብ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ ሁናቴ ፡ በማሳየት ፡ ነው ። ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምናየው ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የተለዩ ፡ ሁናቴዎች ፡ አሉት ።

## የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተገለጠው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ ሕግና ፡ ሕግ ፡ ባልሆኑ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ክፍሎች ፡ ይመደባል ። የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ በአዋጅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ልማድ ፡ ፍርዶች ፡ የሕግ ፡ ሳይንስና ፡ የሕግ ፡ ሰነዶች ፡ በመ

[1] እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሊቆጠሩ ፡ የማይችሉትን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንግሊዞች ፡ በኤርትራ ፡ አቅኚዎች ፡ (ኮሎኒያሊስቶች) ፡ ያወጥዋቸውን ፡ ሕጎች ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ አላገባናቸውም ። (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኘው ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አውሮፓውያን ፡ አቆጣጠር ፡ የተሰጠ ፡ ነው ። የአውሮፓውያን ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ የሰባት ፡ ወይም ፡ የስምንት ፡ ዓመት ፡ ቅድሚያ ፡ ስላለው ፡ ትክክለኛው ፡ ቀን ፡ ባይገኝም ፡ እንኳ ፡ ሰባት ፡ ወይም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ በመቀነስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ፡ ያለውን ፡ አካባቢ ፡ ዘመን ፡ ማወቅ ፡ ይቻላል ።)

ባል ፡ ሊተነተን ፡ ይችላል ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ሳይንስና ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ የሚ ይዝ ፡ ሲሆን ፡ የአገር ፡ ጎብኝዎችን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተደረጉ ፡ ጠቅ ላላ ፡ ጥናቶችን ፡ ጋዜጦችንና ፡ መጽሔቶችን ፡ ይጠቀልላል ። በመግቢያው ፡ የተገ ለጹትን ፡ የዘመን ፡ ክፍሎች ፡ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተልነታቸው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ስናይ ፡ እነዚህን ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ በታሪክ ፡ አንጻር ፡ እናጠናቸዋለን ።

(ሀ) ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ ምንጮች ።

፩ ፤ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ሕጎች ።

ለዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ሕጎች ፡ ማለት ፡ የአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ገዥ ፡ ወይም ፡ ኢንስቲቱሲዮን ፡ የገዥነቱን ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ ፍላጎቱን ፡ ወይም ፡ ሥልጣኑን ፡ በግልጽ ፡ የሚያሳውቅበት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻ ላል ። ይህ ፡ የአዋጅ ፡ ትርጓሜ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ሥልጣን ፡ አይጨምርም ። የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ፍርዶች ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ የሚገኝ ፡ ሕግ ፡ በሚለው ፡ ክፍል ፡ ነው ።

የመጀመሪያውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ስንመለከት ፡ በአዋጅ ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ከሌሎች ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ተለይተው ፡ የሚታ ዩበት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምናየው ፡ በሃይማኖት ፡ መጻ ሕፍት (ይህም ፡ ማለት ፡ ከደንበኞቹ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ውጭ ፡ ከሆኑ ፡ ነገሮች) ፡ ወይም ፡ ከነገሥታት ፡ ታሪክ (ክሮኒክል) ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የሚገኙ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ጠቅላላ ፡ ሁናቴ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ይህም ፡ ወደ ፡ ጀርመንኛና ፡ ጣሊያንኛ ፡ [2] የተተረጐመው ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡ የተባለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት (በጠቅላላው ፡ ሃያ ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ይዘዋል) ፤ ከ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የታወጁትን ፡ ሕጎች ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ ይመስ ላል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በተረጋገጠ ፡ አኳኋን ፡ እያንዳንዱ ፡ አዋጅ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የታወጀ ፡ በማለት ፡ የተወሰነ ፡ ቀን ፡ ሊሰጥ ፡ ባይችል ፡ የታወቀው ፡ ኢጣሊ ያዊ ፡ ሊቅ ፡ ጉይዲ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ አዋጆች ፡ በዐምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን (፲፫፻፲፬-፲፫፻፵፬) ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ደግሞ ፡ በፋሲለደስ ፡ ዘመን (፲፮፻፴፪-፲፮፻፷፯) ፡ ነው ፡ የታ ወጁ ፡ ይላል ። አብዛኞቹም ፡ አዋጆች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አቋምና ፡ አስተዳደር (እንደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አባሎች ፡ የሚቀጠሩትን ፡ የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ አቋም ፡ ጭምር ፡ የሚገልጹም ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ክፍሎች ፡ አሉበት) ፤ የሚመለከቱ ፡ ሲሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ አንዳንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉዳዮችን ፡ የያዙ ፡ አንቀ ጾች ፡ ይገኛሉ ፤ ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፤ ሆኖም ፡ እነዚህ ፡ ሥር ዐቶች ፡ የቤተ ፡ መንግሥትን ፡ አባሎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። ለዚህ ፡ የሚከተ ለው ፡ ጥሩ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። "ወግ ፡ አመ ፡ ይከሥሡ ፡ ወይትከሠሡ ፡ ኢቴግ ፡ ኀበ ፡ ቤትሙ ፡ ይዔውዑ ፡ ፈታሕተ" [3] ።

---

[2] ጂ ፡ ቫሬንበርግ ፤ "ስቱዲየን ፡ ዙር ፡ አቢሲኒሼን ፡ ራይህስአርድኒንግ" ፡ "በ «ዛይትሽሪፍት ፡ ፉር ፡ አሲሪዮሎጂ" ፡ ቮሊዩም ፡ ፴ ፡ (፲፱፻፲፮) ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ወደ ፡ ጀርመንኛ ፡ የተተረጐመውን ፡ ተመልከት ፤ ደግሞ ፡ የኢጣሊያንኛውን ፡ ትርጉም ፡ በኢ ፡ ጉይዲ ፡ "ኮንትሪቡቲ ፡ አላ ፡ ስቶሪያ ፡ ሌቴራሪያ ፡ ዲ ፡ አቢሲኒያ ፡ ኢል ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡» በ ፡ ሬንዲኮንቲ ፡ ዴላ ፡ ሬአሌ ፡ አካዴሚያ ፡ ዴይ ፡ ሊንቼዩ ፡ ሼንዜ ፡ ሞራሌ ፡ ቮሊዩም ፡ ፴፩ ፡ ሴሪ ፡ ፭ ፡ (፲፱፻፳፪) ፡ ገጽ ፡ ፷፭ ፡ ተመልከት ።

[3] ባሬንበርግ ፤ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፲፯ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡ ከተሰበሰቡት ፡ አዋጆች ፡ በቀር (ምናልባት ፡ ሌሎች ፡ የአዋጆች ፡ ጉባኤ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል) ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሕጎች ፡ ከደንበኞቹ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ውጭ ፡ በሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የሚገኙ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በየጊዜው ፡ እየገለበጡ ፡ ከመጽሐፋቸው ፡ አግብተዋቸው ፡ ይገኛሉ ።

ለዚሁ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የታወጁ ፡ ሕጎች ፡ በዘመን ፡ ንግሣቸው ፡ ወይም ፡ በቀደሙት ፡ ነገሥታት ፡ የተፈጸሙትን ፡ ነገሮች ፡ በያዘው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። የሕጎቹም ፡ አጻጻፍ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ኃይለ ፡ ቃላቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ቢገኙም ፡ ትእዛዝነታቸው ፡ ጎልቶ ፡ እንዳይታይ ፡ ለዘብ ፡ ባለ ፡ ሁናቴ ፡ ነው ፡ የሚገለጡት ። የሚከተሉት ፡ ጥቅሶች ፡ ሁለቱንም ፡ ሁናቴዎች ፡ ሊያስረዱ ፡ ይችላሉ ። የመጀመሪያው ፡ ጥቅስ ፡ ክሮኒክል ፡ አፍ ፡ ፓሪስ ፡ ከተባለው ፡ ባሴ ፡ ኤቱድ ፡ ኤትዮፕዬን ፡[4] በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ካሳተመው ፡ የተቀዳ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሕግ ፡ የታወጀበት ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ የያዘ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ በአገሪቱ ፡ የቀድሞው ፡ የሃይማኖት ፡ እምነት ፡ ተመልሶ ፡ ንጉሡ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከዙፋን ፡ የወረደበት (፲፮፻፯—፲፮፻፴፪) ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። የአዋጁ ፡ ቃል ፡ ይኸው ፡—

"አሚን ፡ ይትመይጥ ፡ ወይንግሥ ፡ ፋሲል" ።

ሁለተኛው ፡ ጥቅስ ፡ የተቀዳው ፡ አብሬቪትድ ፡ ክሮኒክል ፡ ከተባለው ፡ ቤጉኖ ፡[5] ካሳተመው ፡ ነው ። ቤጉኖ ፡ ንጉሡ ፡ ዘድንግል (፲፮፻፫—፲፮፻፬) ፡ ያወጀውን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ነው ፡ የጻፈው ፤ የአዋጁም ፡ ቃል ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፡—

"ሰብእ ፡ ሐራ ፤ ወገባር ፡ ምድር ። ወሐረ ፡ ምድረ ፡ ጐዣም ፡ ወተፃብአ ።" ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ በዚህ ፡ ጥቅስ ፡ ላይ ፡ አስተያየት ፡ ሲሰጥ ፡ አዋጆቹ ፡ ከተለመዱት ፡ ዐይነት ፡ የተለዩ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ፡ አጥብቆ ፡ ይናገራል ። እንደ ፡ ተለመደው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ወንዶች ፡ ጦርነት ፡ ሲዘምቱ ፡ መሬት ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ይሆን ፡ ነበር ።[6] ሮሲኒ ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ስለዚሁ ፡ አዋጅ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ሲናገር ፡ ቸሩሊ ፡[7] የተባለ ፡ ሌላ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ ሊቅ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ ይቃወማል ። ቸሩሊ ፡ የአዋጁ ፡ አጠራጣሪነት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ለራሱ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ትርጉም ፡ ለመስጠት ፡ እንዲመቸው ፡ መንግሥት ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ ነው ፡ ይላል ።[8]

በይበልጥ ፡ ለየት ፡ ያሉ ፡ ደግሞ ፡ መጽሐፈ ፡ ምላድ ፡ በተባለው ፡ የንጉሥ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ (፲፬፻፴፬—፲፬፻፷፰) ፡ መጽሐፍ ፡ የሚገኙ ፡ አዋጆች ፡ ናቸው ።

---

[4] ኤር ፡ ባሴ ፤ ኤቱድ ፡ ኤቲዮፒየን ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፰፻፹፩) ፡ ገጽ ፡ ፳፱ ።

[5] ሲ ... ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ ከታች ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፰፻፮ ፡ እና ፡ ፰፻፯ ።

[6] ሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ "ዱዌ ፡ ስኳርቺ ፡ ኢኔዲቲ ፡ ዲ ፡ ክሮናካ ፡ ኤቲዮፒካ-በ ፡ ሬንዲኮንቲ ፡ ዴላ ፡ ሬአሌ ፡ አካዴሚያ ፡ ዴይ ፡ ሊንቼዩ ፡ ሼንዚ ፡ ሞራሌ ፡ ቮሊዩም ፡ ፪ ፡ ሴሪ ፡ ፭ (፲፰፻፺፫) ፡ ከገጽ ፡ ፰፻፲፩ ፡ እስከ ፡ ፰፻፲፪ ።

[7] ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ "ሱዌ ፡ ዱዌ ፡ ፍራዚ ፡ ዴላ ፡ ክሮናካ ፡ አብሬቪያታ ፡ ዴኢ ፡ሬ ፡ ዲ ፡ ኢትዮፒያ ፡" በአናሊ ፡ ዴል ፡ ኢስቲቱቶ ፡ ኦሪየንታሌ ፡ ዲ ፡ ናፖሊ ፡ ቮሊዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፵፱) ከገጽ ፡ ፱፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፱፻፺ ፡ ከኤ ፡ ቸሩሊ ፤ ኢትዮፒያ ፡ ኦቺዴንታሌ ፡ ቮሊዩም ፤ ፩ (ሮማ ፡ ፲፱፻፴) ፡ ከገጽ ፡ ፩፻፴፰ ፡ እስከ ፡ ፩፻፵ ፡ ከተጻፈው ፡ አስተያየው ።

[8] ኤ ፡ ቸሩሊ ፤ አላይ ፡ በ፯ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፪፴፱ ።

አብዛኞቹ፣ የሃይማኖት ፣ ጉዳይ ፣ የሚመለከቱ ፣ ናቸው ፤ ሆኖም ፣ የዘመኑን ፣ መናፍቃን ፣ በሚያወግዙት ፣ ክፍሎች ፣ ውስጥ ፣ አልፈው ፣ አልፈው ፣ ስለ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ ወንጀል ፣ ጉዳይም ፣ የተጻፉ ፣ አሉ ።[9]

እስካሁን ፣ የተመለከትናቸው ፣ አዋጆች ፣ በታወጁበት ፣ ዘመን ፣ ለመላው ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ ፣ ተፈጻሚ ፣ እንዲሆኑ ፣ የወጡ ፣ ናቸው ። ነገር ፣ ግን ፣ ለአንዳንድ ፣ የግል ፣ ሰዎች ፣ ብዙ ፣ ጊዜም ፣ ለአንዳንድ ፣ ድርጅቶች ፣ ልዩ ፣ መብቶች ፣ የሚሰጡትን ፣ የተለዩ ፣ ሕጎችንም ፣ ከዚህ ፣ ጋር ፣ ልንመለከታቸው ፣ ይገባል ። ከእንደዚህ ፣ ያሉትም ፣ ውስጥ ፣ ለምሳሌ ፣ ልዩ ፣ መብት ፣ ወይም ፣ ቻርተር ፣ እየተባሉ ፣ ከሚጠሩት ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ የተጠቀሱ ፣ ሁለት ፣ ጽሑፎች (ዶኩማዎች) ፣ አሉ ። የመጀመሪያው ፣ የተጠቀሰው ፣ የገንዘብ ፣ መዋጮ ፣ ከሚያዙት ፣ እንዲሁም ፣ በሰሜን ፣ ኢትዮጵያ ፣ ለሚገኙ ፣ ገዳማት ፣ ስጦታዎችን ፣ ከሚያደርጉት ፣ ከመቶ ፣ በላይ ፣ ከሚሆኑ ፣ በጣም ፣ ከፍተኛ ፣ ከሆኑት ፣ የጽሑፍ ፣ ጉባኤ ፣ ውስጥ ፣ ነው ። ጽሑፎችን ፣ ባለንበት ፣ መቶኛ ፣ ዓመት ፣ መጀመሪያ ፣ ላይ ፣ ሊበር ፣ አክሱም ፣ በሚል ፣ ስያሜ ፣ ኮንቲ ፣ ሮሲኒ ፣[10] አሳትሟቸዋል ። አሁን ፣ የምንጠቅሰው ፣ ከነዚሁ ፣ ጽሑፎች ፣ ውስጥ ፣ ቀደም ፣ ካሉት ፣ አንዱን ፣ በ፲፬ኛው ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ መጨረሻ ፣ ወይም ፣ በ፲፭ኛው ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ መጀመሪያ ፣ የወጣውን ፣ ሲሆን ፣ ቃሉም ፣ የሚከተለው ፣ ነው ።[11]

"በአኰቴተ ፣ አብ ፣ ወወልድ ፣ ወመንፈስ ፣ ቅዱስ ። አነ ፣ ንጉሥ ፣ ዳዊት ፣ ጕለትኩ · ጕልተ ፣ ለአቡየ ፣ አሮን ፣ ዘደብረ ፣ ኀርም ፣ እዳ ፣ አባ ፣ አሮን ፣ በምልአ ፣ ወአዲ ፣ አውላይ ፣ ክቱር ፣ ዓድ ፣ ጕዕዱድ ፣ ዓድ ፣ ጤቆ ፣ ወራኅራኅ ፣ አዲ ፣ ጸጓር ፣ ማይ ፣ ቊርበት ፣ ማይ ፣ አልባ ፣ ዓድ ፣ አሮን ። እሉ ፣ ኵሎሙ ፣ ዘምድረ ፣ አድያበ ። ወጕድፎ ፣ ዘሀለወት ፣ በጽንፈ ፣ ሰመማ ። ወእምድረ ፣ ጸለምት ፣ ክትር ፣ ወዓድ ፣ አብርሃም ። ከመ ፣ ይኩነኒ ፣ መርሐ ፣ ለመንግሥተ ፣ ሰማያት ። እመቦ ፣ ዘሔደ ፣ ወዘተዓገለ ፣ ውጉዘ ፣ ለይኩን ፣ በሥልጣነ ፣ ጴጥሮስ ፣ ወጳውሎስ ፣ ወበአፈ ፣ አብ ፣ ወወልድ ፣ ወመንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ወበአፈ ፣ ኵሎሙ ፣ ነቢያት ፣ ወሐዋርያት ፣ ለዓለመ ፣ ዓለም ።"

እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ የተመዘገቡ ፣ ሰነዶች ፣ በኢትዮጵያ ፣ ሕግ ፣ ታሪክ ፣ ዘመን ፣ ሁሉ ፣ እስከ ፣ ቅርቡ ፣ ጊዜ ፣ በ፲፱ኛው ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ውስጥ ፣ እንኳ ፣ የወጡ ፣ ይገኛሉ ፤ ሆኖም ፤ በዚሁ ፣ በሊበር ፣ አክሱም ፣ በተገኘው ፣ አንድ ፣ ማስረጃ ፣ ለማወቅ ፣ እንደ ፣ ተቻለ ፣ ስለ ፣ ቻርተር ፣ የሆነ ፣ እንደሆን ፣ በቅርቡ ፣ የታወጁት ፣ ብዙውን ፣ ጊዜ ፣ እነዚያኑ ፣ ቀድሞ ፣ የተሰጡ ፣ ልዩ ፣ መብቶችን ፣ የሚያረጋግጡ ፣ ናቸው ። ከእንደዚህ ፣ ያሉትም ፣ የታወጀው ፣ በመጀመሪያው ፣ የሕግ ፣ ታሪክ ፣ ዘመን ፣ መጨረሻ ፣ ላይ ፣ በንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ዮሐንስ ፣ ፬ኛ ፣ ከ፲፰፻፷፬ ፣ ዓ. ም. እስከ ፣ ፲፰፻፹፩ ፣ ዓ. ም. ባለው ፣ ጊዜ ፣ ነው ። ቃሉም ፣ ይከተላል ።

"ወአነሂ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ዮሐንስ ፣ ሐደስኩ ፣ ኵሎ ፣ ርስተ ፣ ወጉልተ ፣ ዘደብረ ፣ ቢዘን ፣ ዘወሀብዎ ፣ አበውየ ፣ ነገሥታት ፣ ዳዊት ፣ ወዘርአ ፣ ያዕቆብ ፣ ልብነ ፣ ድንግል ፣ ወገላውዴዎስ ። ዘሄደ ፣ ወዘተአገለ ፣ ውጉዘ ፣ ለይኩን ፣ በአፈ ፣

---

9 ኬ ፣ ዌንድ ፤ ዳስ ፣ መስሐፈ ፣ ምላድ (ሊበር ፣ ናቲቪታቲስ) ፣ ኡንድ ፣ መስሐፈ ፣ ሥላሴ ፣ (ሊበር ፣ ትሪኒታቲስ) ፣ ዴስ ፣ ካይዘረስ ፣ ዘርዓ ፣ ያዕቆብ (መጽሐፈ ፣ መዕላድና ፣ መጽሐፈ ፣ ሥላሴ) ፣ ቮሊዩም ፣ ፩ ፣ (ሉቨ ፣ ፲፱፻፷፪) ፤ እና ፣ ሲ ፣ ኮንቲ ፣ ሮሲኒ ፤ እና ፣ ኤል ፣ ሪየቺ ፤ ኢል ፣ ሊብሮ ፣ ዴላ ፣ ሉቼ ፣ ዴል ፣ ንጉሥ ፣ ዘርዓ ፣ ያዕቆብ (መስሐፈ ፣ ብርሃን) ፤ ቮሊዩም ፣ ፩ ፣ (ሉቨ ፣ ፲፱፻፷፬—፲፱፻፷፭) ።

10 ኮንቲ ፣ ሮሲኒ ፤ ሊበር ፣ አክሱም (ፓሪስ ፣ ፲፱፻፱—፲፱፻፲) ።

11 በዚያው ፣ መጽሐፍ ፣ ገጽ ፣ ፳፪ ።

አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እመሂ ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ወእመሂ ፡ ባሕረ፡ ነጋሢ ፡ ወአፈ ፡ መኰንን ። ውጉዛነ ፡ ይኩኑ ፡ በሥልጣነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ።'' 12

ለግል ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለድርጅቶች ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ቻርተር ፡ ከሚ ሰጡት ፡ አዋጆች ፡ ሌላ ፡ ከሕግ ፡ የሚገኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ኢትዮጵያ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ካደረገቻቸው ፡ የኢንተርናሺናል ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የኢንተርናሺናል ፡ ውሎች ፡ የተደረጉ ፡ በመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ገደማ ፡ ሲሆን ፡ ከነዚህም ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ በ፲፰፻፴፫ና ፡ ፲፰፻፵፩ ፡ ዓ.ም. በኢትዮጵያና ፡ በእንግሊዝ ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ የንግሥት ፡ ቪክቶሪያ ፡ መንግሥት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋር ፡ ሁለተኛውን ፡ ከራስ ፡ ዓሊ ፡ ጋር ፡ የተዋዋልዋቸው ፡ ናቸው ።[13] እነዚህ ፡ ውሎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የወዳጅነትና ፡ የንግድ ፡ ውሎች ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩ ፡ ሲሆኑ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ አካባቢ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ የአውሮፓውያን ፡ የፖለቲካ ፡ ጉዳይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እያየለች ፡ በመሄድዋ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉቱ ፡ ውሎች ፡ በሚከተሉት ፡ ዓመታት ፡ እየበረከቱ ፡ ሄዱ ። በመጀመ ሪያ (በ፲፰፻፴፫ ፡ እና ፡ ፲፰፻፵፩ ፡ ዓ.ም. እንደ ፡ ተደረጉት ፡ ውሎች ፡ እንዲሁም ፡ በ፲፰፻፹፩ ፡ ዓ.ም. ምኒልክ ፡ ያደረጉት ፡ የኢትዮጵያና ፡ የጣሊያን ፡ ውል ፡ ሳይ ቀር) ፡ ውሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚደረጉት ፡ በክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ንጉሥና ፡ በውጪ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከሆኑ ፡ ወዲህ ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያሉትን ፡ ውሎች ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ መካከል ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ።[14]

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ የሚመለከቱ ፡ የኢንተርናሺናል ፡ ሕግ ፡ ፕሮብሌሞችንም ፡ ቢሆን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአገሩ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ውጤት ሊያስከትሉ ፡ የሚችሉ ፡ አንቀጾችን ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፡ የ፲፰፻፵፩ ፡ ውል ፡ አንቀጽ ፡ ፲፯ ፡ በኢትዮጵያ (በራስ ፡ ዓሊ ፡ ግዛት) ፡ በእንግሊዝ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቋቁማል ።[15] በተጨማሪም ፡ እነዚህ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉ ፡ ሰነዶች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ፡ በሆኑ ፡ አገሮች ፡ የሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አርሺቮች ፡ እንዲገኙ ፡ አድርገ ዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ በአማርኛና ፡ በተዋዋዩ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተ ጻፉ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በየቋንቋው ፡ የተጻፈው ፡ የውሉ ፡ ቃል ፡ ይለያያል ። ይህም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከባድ ፡ የትርጉም ፡ ችግር ፡ ከመፍጠሩ ፡ በላይ ፡ አንዳንዶቹም ፡ ተዋዋዮችን ፡ አገሮች ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ አድርስዋቸዋል ።

በመጨረሻም ፡ የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያወጣቸውንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተቀበለቻቸውን ፡ ሕጎች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መጥቀስ ፡ ያስፈል

---

12 በዚያው ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፷፮ (ስድሳ ፡ ስድስት) ።

13 የነዚህ ፡ ትራቲዎች ፡ ሁለተኛው ፡ በ ፡ ትራታቲ ፡ ኮንቬንዚዎኒ ፡ ኤ ፡ አኮርዲ ፡ ሬላቲቪ ፡ አል ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ታትሟል ፤ ፬ ፡ ቮሊዩሞች ፡ ሮማ ፡ ፲፱፻፭—፲፱፻፮ ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፰ ፡ እስከ ፡ ፪፻፲ ።

14 ይህንን ፡ የጻፍነው ፡ ዓጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በ፲፰፻፵፯ ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ግዴታ ፡ ሊያ ገቡ ፡ የሚችሉ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ሊዋዋሉ ፡ የሚችሉ ፡ መሆኑን ፡ እያወቅን ፡ ነው ። ሆኖም ፤ ዓጼ ፡ ምኒልክ ፡ በ፲፰፻፹፩ ፡ ከኢጣሊያን ፡ ጋር ፡ ውሉን ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ዮሐንስ ፡ ፬ኛ ፡ በአገሩ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ነበሩ ።

15 እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ በ ፡ ትራታቲ ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፲፪ ፡ ተመልከት ።

ጋል ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ሲኖዶስ ፡ ባለው ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ፤ በከፊል ፡ ታትመዋል ፤ አንዳንዶቹም ፡ ተተርጉመዋል ።[16] በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያትን ፡ በዲዳስቃሊያ ፡ አፖስቶሎ ፡ አማካይነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀብላዋለች ። ግብረ ፡ ሐዋርያትም ፡ የተተረጐመ ፡ በመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ ነው ።[17]

እዚህ ፡ ላይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ታወጁት ፡ ሕጎች ፡ እንደመድማለን ። በጣም ፡ ከፍ ፡ ካሉ ፡ አንዳንድ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከታወጁት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ከታወጁትና ፡ ከጥቂቶቹ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ በቀር ፡ በዘመኑ ፡ የታወጁት ፡ ሕጎች ፡ በሚገባ ፡ አልታወቁም ። በመጀመሪያ ፡ ነገር ፡ ምንጮቹ ፡ ሁሉ ፡ በተለይም ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት (ክሮኒክሎች) ፡ ሕጎች ፡ ተጠቅሰው ፡ ይገኙባቸው ፡ እንደሆነ ፡ ገና ፡ አልተመረመሩም ። ሁለተኛ ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ የሚገኙት ፡ ጽሑፎች ፡ በታሪከ ፡ ነገሥት (ክሮኒክል) ፡ ስለ ፡ ተጠቀሱት ፡ ሕጎች ፡ ትክክለኛነት ፡ ምንም ፡ ማረጋገጫ ፡ አይሰጡ ። እንዳየነው ፡ ሕጉ ፡ የተጻፈበት ፡ ቃል ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ሊተረጐም ፡ የሚችል ፡ ነው ። ይህም ፡ ቸሩሊ ፡ እንደሚለው ፡ ገዥዎቹ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ያደረጉትም ፡ ነገር ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ታሪክ ፡ መዝጋቢዎች (ክሮኒክለር ፤ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ዋናው ፡ ታሪክ ፡ መዝጋቢ ፡ ሹም) ፡ ካለመጠንቀቁ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ እንደሆን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መታወቅ ፡ አለበት ፤[18] በተጻፉበት ፡ ዘመን ፡ በደንብ ፡ የተደራጀ ፡ አርሺቭ ፡ ስላልነበረ ፡ ምናልባት ፡ ምክንያቱን ፡ ለማወቅ ፡ ጨርሶ ፡ አይቻል ፡ ይሆናል ። በተጨማሪ ፡ ከሰነዶቹ ፡ አንዱ ፡ እንደሚያረጋግጠው ፡ ሕግ ፡ እንዲታወቅ ፡ የሚደረገው ፡ አዋጅ ፡ በማስነገር ፡ ነው ። አሁን ፡ የምንጠቅሰው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከተነገረው ፡ አቨሬቤትድ ፡ ክሮኒክል ፡ ከተባለው ፡ የተቀዳውን ፡ የዘድንግልን ፡ ሕግ ፡ ነው ። ከአዋጁ ፡ ቃል ፡ በፊት ፡ የሚከተለው ፡ ይገኛል ።

"ንጉሥ ፡ ዘድንግል ፡ በ፩ ፡ ዓመት ፡ አንገረ ፡ አዋጅ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ . . . . ."[19]

በመጨረሻም ፡ የምንለው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ሕጉን ፡ የሚገልጹልን ፡ አዋጁን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ አዋጅ ፡ አውጥትዋል ፡ እያሉ ፡ አስተያየት ፡ በመስጠት ፡ ነው ።[20] ይህም ፡ ፕሮብሌም ፡ ለሕግ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሰፊ ፡ የጥናት ፡ ክፍል ፡ ይከፍትላቸዋል ።

በሁለተኛው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ሕጎች ፡ አቀራረባቸው ፡ ከአውሮፓውያን ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ አስተሳሰብ ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ አውሮፓዊ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ ከለመደው ፡ ሁናቴ ፡ ጋርም ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ ከታወጁት ፡ በጣም ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። ከነዚህም ፡ የመጀመሪያው ፡ ጽሑፍ (ዶኩማ) ፡ አዲስ ፡ የተሾ

---

16 ስለ ፡ ሲኖዶስ ፡ በ ፡ ጉዌሬርና ፡ ግሬቦ ፡ ማውሮ ፡ ዴ ፡ ሌዎኒሳ ፡ ጉዊሪየ ፡ ሆርነር ፡ ዱሌንሲ ፡ ጉይዲና ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ሕጎች (የመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕጎች) ፡ በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ተመልከት ።

17 ስለ ፡ ዲዳስቃሊያ ፡ የፒል ፡ ፕላትንና ፡ የፍራንሶን ፡ ጥናት ፡ እዚያው ፡ ተመልከት ።

18 ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ዲ ፡ ለቪን ፡ "አምቢጊቲ ፡ አንድ ፡ሞዴርኒቲ ፡" ፊፍስ ፡ ዎርልድ ፡ ኮንግሬስ ፡ አፍ ፡ ሶሾሎጂ ፡ ዋሽንግተን ፡ (፲፱፻፷፱) ፡ ተመልከት ።

19 እላይ ፡ በ፮ኛው ፡ በማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ ገጽ ፡ ፰፻፮—፰፻፯ ፡ ተመልከት ።

20 ለምሳሌ ፡ በ፬ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ኤር ፡ ባሴ ፡ ንጉሥ ፡ አምደ ፡ ጽዮን ፡ ዓላማውን ፡ የተቃወሙትን ፡ ዳኞች ፡ ለማስወገድ ፡ ስላወጣው ፡ አዋጅ ፡ ጠቅሶ ፡ በጻፈው ፡ በገጽ ፡ ፻፩ ፡ ተመልከት ።

ሙትን ፡ የካቢኔት ፡ ሚኒስትሮች ፡[21] የእያንዳንዱን ፡ ሚኒስትር ፡ ሥራ ፡ የሚወስኑ ፡ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ.ም. የወጡትን ፡ አዋጆች ፡ የያዘው ፡ ነው ። ይህ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ሹመት ፡ ዓፄ ፡ ምኒልክ ፡ የአገሪቱን ፡ አስተዳደር ፡ እንደ ፡ አውሮፓውያን ፡ ለማድረግ ፡ ከወሰዱት ፡ የመጀመሪያ ፡ እርምጃ ፡ አንዱ ፡ ሲሆን ፡ ሌሎችም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ተከትለውታል ። ለዚህ ፡ የሚሆነውን ፡ ማስረጃ ፡ ባላምበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ በዝክረ ፡ ነገር ፡[22] አቅይተውናል ።

እላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሕጎች ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ ውርስና ፡ ስለ ፡ አዲስ ፡ ገንዘብ ፡ መውጣት ፡ የታወጁትንም ፡ እንጠቅሳለን ። እንደዚሁም ፡ በአቀራረባቸው ፡ የጥንቱ ፡ ነገሥታት ፡ በሚያውጁት ፡ ዐይነት ፡ የወጡ ፡ ሕጎችም ፡ አሉ ።[23] ለዚህ ፡ ጥሩ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ.ም. በሐረር ፡ የታወጀውና ፡ በ ፡ ለ ፡ ሴሜር ፡ ዲ ፡ ኤቲዮፒ ፡ የታተመው ፡ ነው ። ቃሉም ፡ ይከተላል ። "እላንት ፡ ክርስቲያኖችና ፡ እስላሞች ፤ እንደ ፡ እምነታችሁ ፡ ለመኖር ፡ ነጻ ፡ ናችሁ ። ማንም ፡ ሰው ፡ በደል ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ለኛ ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ማንም ፡ ሰው ፡ የሕዝብን ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ የሚያበላሽ ፡ ወሬ ፡ እንዳያወራ ፡ ይሁን" ።[24]

በመጨረሻም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሕግ ፡ ማውጣትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተጀመረ ፡ ይመስላል ። ይኸውም ፡ ለምሳሌ ፡ ከፖስታ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፖስታ ፡ ደንብ ፡ የወጣው ፡ የሕዝብ ፡ ማስታወቂያ ፡ ነው ። ይህ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሕግ ፡ አዲስ ፡ ከተቋቋሙት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለክፍሉ ፡ ኃላፊ ፡ በሆነው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ኤክስፐርት ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ ፖስታና ፡ ቴሌግራም ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ጊል ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ደንቡን ፡ ለሕዝብ ፡ ያስታውቅ ፡ ነበር ።[25]

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ታወጀው ፡ ሕግ ፡ በይበልጥ ፡ ብናውቅም ፡ በታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በአገር ፡ ጎብኝዎች ፡ ጽሑፍና ፡ በሌሎችም ፡ የተጠቀሱ ፡ ገና ፡ የማናውቃቸው ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ አዋጆች ፡ አሉ ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ የጻፉት ፡ ታሪክ ፡ መንግሥት ፡ በዓጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ስለወጡት ፡ ሕጎች ፡ ብዙ ፡ ቦታ ፡ ስለሚያወሳ ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።[26]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ካየናቸው ፡ አጠቃላይ ፡ አዋጆች ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ የወጡ ፡ አዋጆችም ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ የኮንሲሲዮን ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ናቸው ።

በአገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሁሉ ፡ የታወቀ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ለአንድ ፡ ግል ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የኮንሴሲዮን ፡ ውል ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ ያየናቸውን ፡ ቻርተሮች ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ይመስላል ። ስለ

---

21 ሰላሙ ፡ በቀለና ፡ ዶ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ መግቢያ ፤ ስለ ፡ መጀመሪያዎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሚኒስትሮች ፡ "በቅርቡ ፡ በሚታተመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ተመልከት ።

22 አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፩ ።

23 ስለተጠቀሱት ፡ አዋጆች ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ባላምበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ገጽ ፡ ፸፪ ፡ (ስለ ፡ ውርስ) ፡ ገጽ ፡ ፻፺፱ ፡ (ስለ ፡ አዲስ ፡ ገንዘብ ፡ መውጣት) ፡ ተመልከት ።

24 ለ ፡ ሰሜር ፡ ዲትዮፒ ፤ ኦገስት ፡ ፲፱፻፷ ፡ ፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፯ ።

25 ለ ፡ ሰሜር ፡ ዲትዮፒ ፡ ኖቬምበር ፡ ፲፱፻፷ ፡ ፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፷፫ ።

26 ገብረ ፡ ሥላሴ ፤ ክሮኒክ ፡ ዱ ፡ ሬኘ ፡ ደ ፡ ሚኒልክ ፡ ደ ፡ ሯ ፡ ዲ ፡ ሯ ፡ ዲትዮፒ ፤ ፪ ፡ ቮሊዩሞች ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፴፪) ፤ ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ ዳኞች ፡ መሾም ፡ ቮሊዩም ፡ ፪ ፡ ከገጽ ፡ ፭፻፴፩ ፡ እስከ ፡ ፭፻፴፪ ፡ ተመልከት ።

ዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ሰነድ ፡ ለመስተር ፡ ሴን ፡ የተሰጠ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ነው ። ኮንሴሲዮኑ ፡ ለመስተር ፡ ጆርጅ ፡ ዊሊያም ፡ ሴንና ፡ በሎንዶን ፡ ከተማ ፡ ለሚኖሩ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጆች ፡ ባልንጀሮቹ ፡ የማዕድን ፡ ኮንሲሲዮን ፡ የተሰጣቸው ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ።[27] እርግጥ ፡ ነው ፡ የጥንቱ ፡ ዐይነት ፡ ልዩ ፡ መብቶችና ፡ ቻርተሮች ፡ በዓጼ ፡ ምኒልክም ፡ ዘመን ፡ ነበሩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለባቸው ፤ ኮንሲሲዮኖቹ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በኤኮኖሚ ፡ ለማሳደግ ፡ ለተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ዋና ፡ ማስረጃዎችና ፡ ፍጹም ፡ እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። ከኮንሴሲዮኖቹ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የተጣለባቸው ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ሆነ ፡ በአውሮፓ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ እየተደጋገሙ ፡ ይወጣሉ ፤ ለምሳሌ ፡ በ"ዝክረ ፡ ነገር" ፡ "ኢትዮጵያ ፡ በአውሮፓ ፡ ፖለቲክ" ፡[28] በተባለው ፡ በፒሊ ፡ መጽሐፍ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት" ፡[29] በተባለው ፡ የዚርቦስ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጠቅሰዋል ። ከዋናዎቹም ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ ለምሳሌ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከፍተኛ (ተደማጭ) ፡ አማካሪ ፡ ለአልፍሬድ ፡ ኤልግ ፡[30] የተሰጠው ፡ የባቡር ፡ ሀዲድ ፡ ኮንሴሲዮንና ፡ ለግብፅ ፡ ብሔራዊ ፡ ባንክ ፡[31] የተሰጠው ፡ የሀበሻ ፡ ባንክ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ናቸው ። እርግጥ ፡ ነው ፡ እላይ ፡ እንደ ፡ ተጠቀሰው ፡ ለመስተር ፡ ሴን ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ያሉ ፡ አነስተኛ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ለሌሎች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎችም ፡ የተሰጡ ፡ አሉ ። ሆኖም ፡ እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሁለት ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ የእንደዚህ ፡ ያሉቱ ፡ መብቶች ፡ መሰጠት ፡ በአገሪቱ ፡ ላይ ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ለውጥ ፡ ገልጸው ፡ ያሳያሉ ። አነስተኞቹ ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በአውሮፓ ፡ አርሺቮች ፡ ነው ፡ የሚገኙ ፤ ገና ፡ የሚጠኑና ፡ የሚመረመሩ ፡ ናቸው ።[32]

ኢትዮጵያ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ኩባንያዎችና ፡ የግል ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ውል ፡ ማድረግ ፡ በጀመረችበት ፡ ጊዜ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታትም ፡ ጋር ፡ ያላት ፡ ግንኙነት ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ግንኙነቶች ፡ እንዲበዙ ፡ ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ እንዲኖሩ ፡ ያደረጉት ፡ ምክንያቶች ፡ ዓጼ ፡ ምኒልክ ፡ ከውጪ ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ የነበራቸው ፡ ፈቃደኝነትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአፍሪካ ፡ ቀንድ ፡ ያላት ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ናቸው ። አንዳንዶቹ ፡ ውሎች ፡ ለዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ዘመናዊ ፡ ታሪክ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚዎች ፡ ናቸው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ በሁለተኛው ፡ የሕግ ፡

---

27 ፐብሊክ ፡ ሬከርድ ፡ ኦፊስ ፡ አርካይቭስ ፡ ኤፍ ፡ ኦ ፡ ፻፴፯ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የነበረው ፡ ቆንሲል ፡ ጂ ፡ ኤል ፡ ሀሪንግተን ፡ ጥር ፡ ፳ ፡ ፲፱፻ ፡ ለላሲስበሪ ፡ ማርክዊስ ፡ የጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ አባሪ ።

28 በ፳፪ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዝክረ ፡ ነገር ፡ ከገጽ ፡ ፬፻፶፪ ፡ እስከ ፡ ፬፻፹፪ ፡ ስለ ፡ የኢትዮጵያና ፡ ፈረንሳይ ፡ ባቡር ፡ ሐዲድ ፡ ስለ ፡ ተደረጉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ፡ ተመልከት ፤ እንዲሁም ፡ ኤም ፡ ፒሊ ፡ ሊያ ፡ ኤቲዮፒ ፡ ኔላ ፡ ፖሌቲካ ፡ ኤውሮፒያ ፡ (ፓዶቫ ፡ ፲፱፻፴፯) ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፴፬ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፰ ፡ (ለዶክተር ፡ ኢልክ ፡ የተሰጠ ፡ የማዕድን ፡ ኮንሲሲዮን ፡) ገጽ ፡ ፪፻፴፱ ፡ (እንዲሁም ፡ ለአንድ ፡ የኢጣሊያን ፡ ሴንዲካ) ።

29 ኤ ፡ ዜርቦስ ፡ ሌምፒር ፡ ዴትዮፒ ፡ (አቴን ፡ ፲፱፻፴፮) ፡ በገጽ ፡ ፫፻፫ ፡ አንድ ፡ የኮንሴሲዮን ፡ ውሎች ፡ ዝርዝር ፡ ይሰጣል ።

30 ፒሊ ፡ እላይ ፡ በ፳፰ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፲፬ ፡ እንዲሁም ፡ ዜርቮስ ፡ በ፳፱ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፶፱ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷፩ ፡ ተመልከት ።

31 ፒሊ ፡ በ፳፰ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፵፫ ፡ እስከ ፡ ፪፻፵፬ ፤ ዜርቮስ ፡ በ፳፱ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፻፹፭—፻፹፪ ተመልከት ።

32 በኢትዮጵያ ፡ ለዜጎቻቸው ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፡ ኮንሲሲዮኖች ፡ ሁሉ ፡ ለመንግሥታቸው ፡ አንዳንድ ፡ ኮፒ ፡ መላክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኙ ፡ የቆንሲሎች ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ እንደራሴዎች ፡ ልማድ ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ ኮንሲሲዮኑን ፡ በሰጠው ፡ አገርና ፡ ኮንሲሲዮኑ ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ኩባንያ ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ በተፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ ሰውየው ፡ ወይም ፡ ኩባንያው ፡ የውሉን ፡ ግልባጭ ፡ በመላክ ፡ ከአገሩ ፡ መንግሥት ፡ ድጋፍ ፡ ይጠይቅ ፡ ነበር ።

ታሪክ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ዝነኛ ፡ የሆነውን ፡ የውጫሌ ፡ ውልና ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት (በ፯ኛው ፡ አንቀጽ) ፡ መቋቋሙን ፡ በግልጽ ፡ ስለሚያውቅ ፡ የብዙ ፡ ግጭትና ፡ አለመግባባት ፡ ምንጭ ፡ የሆነውን ፡ ከፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ዘግየት ፡ ብሎ ፡ በ፲፱፻፰ ፡ ዓ.ም. የተደረገውን ፡ የኮቡኮስኪ ፡ ውል ፡ ማውሳት ፡ ይበቃል ። የነዚህ ፡ ውሎች ፡ ተፈላጊነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎች ፡ በየጊዜው ፡ ይታተማሉ ፤ በአማርኛ ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ታትመው ፡ የሚገኙ ።[33] እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጽሑፎች (ዶኩማዎች) ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በጣም ፡ ጠቃሚዎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በቅርቡ ፡ ታትመው ፡ እንደሚወጡ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ይህ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ተመራማሪዎች ፡ በየቋንቋው ፡ ስላገኙት ፡ ጽሑፍ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ የሚያደርጉት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ለዘለቄታው ፡ ይወገዳል ።[34]

እንደተመለከትነው ፡ በሁለተኛው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በተለይም ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. በኋላ ፡ በአዋጅ ፡ ስለ ፡ ወጡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ በሰፊው ፡ እናገኝበታለን ። ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ወይም ፡ ከ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ.ም. እስከ ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ ባለው ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አዋጆች ፡ በብዛት ፡ የወጡ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በደንብ ፡ የተዘጋጁና ፡ የተሟሉ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሕጎቹ ፡ በሚገባ ፡ ታውቀዋል ። የተሟሉ ፡ ብዙ ፡ የሕግ ፡ ሰነዶች ፡ ያሉን ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፈው ፡ ይገኛሉ ። አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ የአማርኛው ፡ ሰነድ ፡ ውሉን ፡ ባደረገው ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ወገን ፡ ቋንቋ ፡ ከተጻፈው ፡ ሰነድ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።[35]

በይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ የሚያጓጓው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የአዋጆቹን ፡ መነሻ ፡ ምንጮች ፡ ወይም ፡ የአዋጆቹን ፡ መፍጠሪያዎች ፡ እንደምናገኝ ፡ ያለን ፡ ተስፋ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ ዓጼ ፡ ምኒልክ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የተጻፉትን ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፡ እየገለበጠና ፡ እየመዘገበ ፡ እንዳይጠፉና ፡ እንዳይበላሹ ፡ በጥንቃቄ ፡ መጠበቅ ፡ ከሥራዎቹ ፡ አንዱ ፡ የሆነውን ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ በአዋጅ ፡ በመሾማቸው ፡ ነው ።[36] እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደተገለጠው ፡ ተግባሩ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተወስኖ ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ መሾም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ በተደረገበት ፡ ዘመን ፡ እርምጃው ፡ የተወሰደ ፡ ለወደፊቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሚጠቅም ፡ በሙሉ ፡ ታስቦበት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ባይቻልም ፡ ሹመቱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ በኦፊሴል ፡ እንደማቋቋም ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ።

---

33 በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለሰጠናቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ ይህ ፡ አንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ፒሊም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ትራታቲ ፡ ወይም ፡ ዜርቮስ ፡ ውሎችን ፡ በአውሮፓውያን ፡ ቋንቋ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ በጽሑፎቻቸው ፡ አግብተው ፡ አያውቁም ። ከዚህ ፡ የተለየ ፡ ግን ፡ ሮቢንሰን ፡ ውጫሌ ፡ ፲፮ ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፬ ፡) ተመልከት ።

34 በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የታሪክ ፡ ክፍል ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሩቢንሰን ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ በመሰብሰብ ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ በቅርቡ ፡ ታትሞ ፡ እንደሚወጣ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

35 ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ምሳሌዎች ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግና ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በተሰጡ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ክፍል ፡ በቀር ፡ ሌሎችን ፡ በአማርኛ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ አናገኝም ።

36 ባላምበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በገጽ ፡ ፮፻፵፰ ፡ ተመልከት ።

ሕጉን ፡ ፈጣሪ ፡ ወይም ፡ አውጭ ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ ስለተባለው ፡ ጉዳይ ፡ ከአንዳንድ ፡ አስተዳደርን ፡ ከሚመለከቱ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሕጎች ፡ በስተቀር ፡ የዋናዎቹ ፡ አዋጆች ፡ ፈጣሪ ፡ ወይም ፡ አውጭ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው ። አዲሶቹ ፡ ሚኒስትሮች ፡ አዲስ ፡ አቋሞችና ፡ አዲስ ፡ ስያሜዎችም ፡ ቢሰጣቸው ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ለነዚያው ፡ ለንጉሡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አማካሪዎች ፡ ተመድቦ ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ይመስላል ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በአገሪቱ ፡ የማተሚያ ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ ስለ ፡ ተጀመረ ፡ ሕጉ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚገለጥበት ፡ ሁናቴ ፡ ተለውጥዋል ። በሃያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በድሬዳዋ ፡ ሳያቋርጥ ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ ማተሚያ ፡ ሲኖር (ለ ፡ ሰሜር ፡ ደ ፡ ኤቲዮፒ ፡ የተባለው ፡ ጋዜጣ ፡ በዚሁ ፡ ነበር ፡ የሚታተም) ፡ ጥቂት ፡ ቆየት ፡ ብሎ ፡ በ፲፱፻፲፩ ፡ ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ ፡ መጽሐፎች ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ታተሙ ፤ (ከታተሙትም ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ መጽሐፎች ፡ አንዱ ፡ ዓጼ ፡ ምኒልክ ፡ ስለ ፡ ሾምዋቸው ፡ አዲስ ፡ ሚኒስትሮች ፡ በምሳሌ (አሌጎሪ) ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።)[37] ሆኖም ፡ የተሰጠን ፡ መግለጫ ፡ ትክክለኛ ፡ ከሆነ ፡[38] አዋጆችና ፡ የመንግሥት ፡ ኦፊሴል ፡ ዶኩማዎች ፡ ብቻ ፡ የሚታተሙበት ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ማተሚያ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት (በጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ ክፍል) ፡ እላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ አገልግሎት ፡ በመስጠት ፡ ላይ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። እስከ ፡ ፲፱፻፰ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ አዋጅ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚገለጠው ፡ በዚያው ፡ በጥንቱ ፡ መንገድ ፡ ሲሆን ፡ በጠቅላላውም ፡ በዓፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ከመጀመሪያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተሠርቶበታል ። ለሰሜር ፡ ደ ፡ ኤቲዮፒ ፡ የተባለው ፡ ጋዜጣ ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፰ ፡ ዓ.ም. ባወጣው ፡ እትም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ አዋጅ ፡ ሲነገር ፡ የተፈጸመውን ፡ ሥርዐት ፡ ይገልጻል ።[39] መግለጫውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። አዋጅ ፡ ነጋሪው ፡ አንድ ፡ ግልገል ፡ አንበሳ ፡ "ለንጉሡ ፡ ሥልጣን ፡ ሕያው ፡ ምልክት ፡" አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ይመጣል ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ነጋሪት ፡ ይመታና ፡ አዋጁ ፡ ለሕዝብ ፡ በአማርኛ ፡ ይነበባል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አዋጁ ፡ ወዲያውኑ ፡ በአደርኛ ፡ በጋልኛና ፡ በሶማልኛ ፡ ይተረጎማል ። ስለዚህ ፡ አዋጁ ፡ የተነገረበትን ፡ ቋንቋ ፡ ስለማላውቅ ፡ አዋጁን ፡ አልሰማሁም ፡ በማለት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከሕጉ ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ።

ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ ስንገባ ፡ ከቀደሙት ፡ ዘመናት ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

በመጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የታወጀው ፡ ሕግ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ራስ ፡ ተፈሪ ፡ እንደራሴ ፡ ከተባሉበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ የሃያ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ ከ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ.ም. በኋላ ፡ የሚወጣው ፡ አዋጅ ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ። ተጠብቀው ፡ ከተገኙት ፡ ሰነዶች ፡ ለመረዳት ፡ እንደተቻለው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አዋጆች ፡ ያህል ፡ ይሆናል ።[40]

---

37 ሰላሙ ፡ በቀለና ፡ ጆ ፡ ቫንደርላንደን ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፳፩ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ምሳሌውም ፡ ስለሚገኝ ፡ ተመልከት ።

38 ይህ ፡ መግለጫ ፡ ከባላንበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ በቃል ፡ ነው ፡ የተነገረን ።

39 ለ ፡ ሰሜር ፡ ዴትዮፒ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ።

40 ይህ ፡ ግምት ፡ የተመሠረተው ፡ ሻምበል ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ የብርሃንና ፡ ሰላምን ፡ መጽሔት ፡ ያጠናውን ፤ ባላምበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ በዝክረ ፡ ነገር ፤ ዜርቮስ ፡ በሌምፒር ፡ ዴትዮፒ ፡ ከሰበሰቡት ፤ እንዲሁም ፡ አገር ፡ ጎብኝዎች ፡ ከጻፉትና ፡ ከታሪክ ፡ ጥናት ፡ ውስጥ ፡ ከተገኙት ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃዎች ፡ ጋር ፡ በማስተያየት ፡ ነው ።

ይልቁንም ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ በሕጉ ፡ ጥራትና ፡ መሻሻል ፡ በኩል ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርምጃ ፡ ተደርጓል ። አዋጆቹ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የያዙ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ጉዳይ ፡ ከወጡት ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ አዋጆች ፡ ሌላ (ስለ ፡ ኩባንያዎች ፡ ስለ ፡ መክሰር ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ ደላሎችና ፡ ሌሎችም) ፡ ይልቁንም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የአገሪቱን ፡ መንግሥት ፡ በተወሰነ ፡ አቋም ፡ የሚመሠርተው ፡ የ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወንጀሎችንና ፡ ቅጣቶችን ፡ አጠቃልሎ ፡ የሚወስነው ፡ የ፲፱፻፴ ፡ ዓ.ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ናቸው ።[41] የ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአገሪቱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ የሚያወጣቸውን ፡ የሕግ ፡ ዐይነቶች ፡ እየለየ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ለያዝነው ፡ ጥናት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ በአዋጅና ፡ በድንጋጌ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ተደርጓል ። በቁጥር ፡ ፴፬ ፡ መሠረት ፡ አዋጅ ፡ ማለት ፡ በሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች (በሕግ ፡ መምሪያና ፡ በሕግ ፡ መወሰኛ) ፡ ታይቶ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚጸድቅ ፡ ነው ፤ ድንጋጌ ፡ ደግሞ ፡ በቁጥር ፡ ፱ ፡ መሠረት ፡ አማካሪዎቹ ፡ ባልተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ ሲገጥም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚያወጡት ፡ ሕግ ፡ ነው ። ሆኖም ፤ እንዲያጸድቃቸው ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ፤ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ካላጸደቃቸው ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ይሻራሉ ። በመጨረሻም ፡ በቍጥር ፡ ፲ ፡ መሠረት ፡ ሕጉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ ጸጥታ ፡ እንዲጠበቅና ፡ አገሩ ፡ እንዲበለጽግ ፡ ለማድረግ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያወጡ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ናቸው ።[42] ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ የሚያወጣቸው ፡ ሦስት ፡ ዐይነት ፡ ሕጎች ፡ ተሠርተዋል ፤ እነሱም ፡ አዋጅ ፡ ድንጋጌና ፡ ትእዛዝ ፡ ናቸው ። ከጦርነቱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በሚገኙት ፡ አምስት ፡ ዐመት ፡ ውስጥ ፡ የወጡት ፡ አብዛኞቹ ፡ ሕጎች ፡ ሦስቱንም ፡ ዓይነት ፡ የያዙ ፡ ናቸው ።

በዘመኑ ፡ የዝቅተኛ ፡ ሕግ ፡ ማውጣትም ፡ ሥራ ፡ እያደገ ፡ ሄድዋል ። ዝቅተኛ ፡ ሕግ ፡ በማውጣት ፡ በኩል ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ የያዘው ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ማዘጋጃ ፡ ቤቱም ፡ በየጊዜው ፡ ያወጣቸው ፡ ሕጎች ፡ በከተማ ፡ ስለሚገኙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባሮች ፡ ሲሆን ፡ ካወጣቸውም ፡ ሕጎች ፡ ጥቂቶቹ ፡ ለምሳሌ ፡ ከቸርቻሮች ፡ ስለሚጠየቅ ፡ ግብር ፡ ስለ ፡ ከተማ ፡ ጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ስለ ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ መመዝገብ ፡ ስለ ፡ ሲኒማ ፡ ቴአትር ፡ ቤትና ፡ ሌሎችም ፡ መደሰቻ ፡ ስፍራዎች ፡ ስለ ፡ መቆጣጠር ፡ (ከጣሊያን ፡ ጋር ፡ የነበረውም ፡ ጠብ ፡ እየከረረ ፡ ሲሄድ ፡) ሌሊት ፡ ከኦ ይሮፕላን ፡ ኦ ደጋ ፡ ስለ ፡ መከላከል ፡ ናቸው ።[43] ከማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሌላ ፡ እያንዳንዱም ፡ የሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በየክፍሉ ፡ ትጋት ፡ ያሳይ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያዎች ፡

---

41 ከነጻነት ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ስለ ፡ ተተረጐመው ፡ በ፲፱፻፴ ፡ ስለወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ኤስ ፡ ሎንስታይን ፡ ማቴሪያልስ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ስተዲ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፒናል ፡ ሎ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮፒያ ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፩ ፡) ከገጽ ፡ ፶፰ ፡ እስከ ፡ ፷ ፡ እና ፡ እንዲነበቡም ፡ ስለተጠቀሱ ፡ መጽሐፎች ፡ ከገጽ ፡ ፷፯ ፡ እስከ ፡ ፷፰ ፤ እንዲሁም ፡ የቾሩሲን ፡ ምርምር ፡ "ኢል ፡ ኑዎቮ ፡ ኮዲቼ ፡ ፔናሌ ፡ ኤቲዮፒኮ ፡ ኤድ ፡ ኢ ፡ ሱዎኢ ፡ ፕሪንቺፒ ፡ ፎንዳሜንታሊ" ፡ በ ፡ ኦሪየንቴ ፡ ሞዴርኖ ፡ ቮሊዩም ፡ ፲፪ ፡ (፲፱፻፴፪ ፡) ከገጽ ፡ ፫፻፶፭ ፡ እስከ ፡ ፬፻፭ ፡ ተመልከት ።

42 የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፳፫ ።

43 ስለነዚህ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ደንቦች ፡ ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ፲ ፡ መጋቢት ፡ ፲፱፻፳፫ ፤ ፲፫ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱፻፳፫ ፤ ፲፫ ፡ መስከረም ፡ ፲፱፻፳፬ ፤ ፳ ፡ ነሐሴ ፡ ፲፱፻፳፬ ፤ እና ፡ አእምሮ ፡ ፳፬ ፡ መስከረም ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ተመልከት ።

ይወጡ ፡ ነበር ፤ ለምሳሌ ፡ ከእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለ ፡ አደን ፡ ፈቃድ ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የገንዘብ ፡ ምንዛሪ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መዘዋወር ፡ የሚወጡት ፡ ማስታወቂያዎች ። [44]

እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ዐይነት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎች ፡ በብዛት ፡ መውጣት ፡ ለግል ፡ ሰዎችና ፡ ለኩባንያዎች ፡ [45] ልዩ ፡ መብትና ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ የሚሰጡትን ፡ እንዲሁም ፡ ከውጭ ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ማድረግ ፡ የመሳሰሉትን ፡ የልዩ ፡ ሕጎች ፡ እድገትና ፡ መውጣት ፡ አላስቀረም ። እንዲያውም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለምሳሌ ፡ ከሆላንድና ፡ ከጃፓን ፡ [46] ጭምር ፡ ከብዙ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ውል ፡ በኩል ፡ ሕጉ ፡ በይበልጥ ፡ ተስፋፍትዋል ። በመጨረሻም ፡ ልናስታውሰው ፡ የሚገባ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ሊግ ፡ ኦፍ ፡ ኔሽንስ ፡ [47] ለመግባት ፡ ጠይቃ ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ.ም. አባል ፡ እንድትሆን ፡ ስለ ፡ ተፈቀደላት ፡ ከውጭ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ለማሻሻል ፡ (ምንም ፡ እንኳ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ውጤቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የማያስደስት ፡ ቢሆን ፡) ቁርጠኛ ፡ እርምጃ ፡ ተወስድዋል ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ወጣው ፡ ሕግ ፡ በይበልጥ ፡ ስንመራመር ፡ ሌሎችም ፡ ጠቃሚ ፡ ለውጦች ፡ እናገኛለን ።

በመጀመሪያ ፡ ነገር ፡ አብዛኛው ፡ ሕግ ፡ ሳያቋርጥ ፡ በትንንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ (በተለይም ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያሉት ፡ ሕጎች ፡ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የኩባንያዎች ፡ ሕግ ፡ የመክሰር ፡ ሕግና ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ ያሉት) ፡ ወይም ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ በ፲፱፻፳፭ ፡ ዓ.ም. ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በሚል ፡ ስያሜ ፡ በመሠረቱት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትመው ፡ ይወጡ ፡ ነበር ። ጋዜጣው ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ የሚገለጽበት ፡ ደንበኛ ፡ ጋዜጣ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አይቆጠርም ። ሆኖም ፡ ከመሥራቹ ፡ ዝነኛነት ፡ የተነሳና ፡ በየጊዜውም ፡ በአዋጅ ፡ እንደሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ያሉት ፡ የኦፊሴል ፡ ዶኩማዎች ፡ ስለሚታተሙበት ፡ እንደ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ። [48] ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ የሚታተሙ ፡ጽሑፎች ፡ መበርከት (አንዳንዶችም ፡ ለየብቻ ፡ እየታተሙ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚታደሉ ፡ ሲኖሩ ፤ ለምሳሌ ፡ ለከተማ ፡ ውስጥ ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች) ፡ አዋጅ ፡ በጥንቱ ፡ ዐይነት ፡ መታወጁን ፡ አላስቀሩም ። እንዲያውም ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ ካወጥዋቸው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕጎች ፡ አንዱ ፡ አዋጅ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚነገርበትን ፡ ትክክለኛ ፡ ሥርዐት ፡ የሚወስን ፡ ነው ። ይህ ፡ አዋጆች ፡ ለሕዝብ ፡ የሚነገሩበት ፡ ሥርዐት ፡ ለሚወጡት ፡ አዋጆች ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ባይሆን ፡ እንኳ ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ በር ፡ ከግንቡ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያስታውቃቸውን ፡

[44] ስለነዚህ ፡ በሚኒስቴሮች ፡ ስለወጡ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ፱ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፱፻፳፫ ፤ ፲፪ ፡ ሰኔ ፡ ፲፱፻፳፬ ፡ እና ፡ ፲ ፡ መጋቢት ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ተመልከት ።

[45] ስለነዚህ ፡ ዝርዝሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተሟሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ባንችል ፡ ዜርቮስ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ተመልከት ፤ ያንኑ ፡ በገጽ ፡ ፫፻፱ ፡ እይ ።

[46] ከኒዘርላንድ (ሆላንድ ፡) ጋር ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውል ፡ ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ግንቦት ፡ ፲፱፻፳ ፤ ከጃፓን ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ዜርቦስ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፬፻፹፮ ፡ ተመልከት ።

[47] ለምሳሌ ፡ አ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፕራዴል ፡ ለ ፡ ኮንፍሊ ፡ ኢታሎ ፡ ኢቲዮፒየን (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡) ተመልከት።

[48] በየጊዜው ፡ የወጣውን ፡ የዚህን ፡ ጋዜጣ ፡ ቍጥር ፡ በሙሉ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በብሔራዊ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንኳ ፡ ማግኘት ፡ አልተቻለም ። ከተገኙት ፡ ቍጥሮች ፡ ለመገመት ፡ እንደቻልነው ፡ ይህ ፡ ሳምንታዊ ፡ ጋዜጣ ፡ ከተመሠረተበት ፡ ከጃንዋሪ ፡ ፲፱፻፳፭ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ መጨረሻ ፡ በየሳምንቱ ፡ ሳያቋርጥ ፡ የታተመ ፡ ይመስላል ።

ከፍተኛ ፡ አዋጆች ፡ ይመለከታል ። [48] (ሀ) በዚህም ፡ ዘመን ፡ አዋጅ ፡ በጥንቱ ፡ ዐይነት ፡ እንዲነገር ፡ የተደረገው ፡ ሌላ ፡ ሰፊ ፡ ዘዴ ፡ ባለመኖሩ ፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ስንመለከተው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ በአማርኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ስለታተመ ፡ የመጀመሪያውን ፡ እትም ፡ ለማግኘት ፡ ችግር ፡ በገጠመን ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱ ፡ ቋንቋ ፡ በአንዱ ፡ የታተመውን ፡ አናጣም ። ለምሳሌ ፡ ብዙ ፡ አዋጆች ፡ በባላንበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ዝክረ ፡ ነገር ፡ [49] ውስጥ ፡ በአማርኛ ፡ ታትመው ፡ ሲገኙ ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ በዝክረ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የማይገኙ ፡ ሌኢምፒር ፡ ደ ፡ ኤቲዮፒ ፡ [50] በተባለው ፡ የዚርቦስ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ታትመዋል ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በሦስተኛው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰነዶች ፡ ልናገኝ ፡ በመቻላችን ፡ በአዋጅ ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ በዘመኑ ፡ ከሚገኙት ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ሁሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ መያዙን ፡ ለመገንዘብ ፡ እንችላለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ጋዜጣ ፡ ወይም ፡ የዘመኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ ማውጣት ፡ ተግባራቸው ፡ ያደረጉ ፡ ሁሉ ፡ የዘመኑን ፡ ሕግ ፡ በሙሉ ፡ ይዘዋል ፡ ለማለት ፡ ስለማንደፍር ፡ የሥራችን ፡ ውጤት ፡ ከሞላ ፡ ጎደል ፡ ነው ። ሆኖም ፤ የዘመኑ ፡ ሕግ ፡ ተሟልቶ ፡ እንዲገኝ ፡ በሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ርዳታና ፡ ድካም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የተሟላ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ አለን ። [51]

አሁን ፡ ደግሞ ፡ መነሻው ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተመለሱበት ፡ ከሆነው ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ መግባታችን ፡ ነው ። ዘመኑ ፡ በሕግ ፡ ማውጣት ፡ በኩል ፡ ካለፈው ም ፡ ዘመን ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ለውጦች ፡ ተደርጎበታል ። ለውጦቹ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ዋኖቹን ፡ ብቻ ፡ እንመለከታለን ።

በመጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በአዋጅ ፡ የሚወጣው ፡ ሕግ ፡ በአገሪቱ ፡ የሕግ ፡ እድገትና ፡ መሻሻል ፡ በኩል ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ አዋጅ ፡ ያልወጣበት ፡ የሕግ ፡ ዐይነት ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ። የወጣው ፡ ሕግ ፡ በጣም ፡ የበዛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሕጉን ፡ በአንድነት ፡ ሰብስቦ ፡ ማውጣት ፡ አስፈልጓል ። በአንድነት ፡ የተሰበሰቡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ በማንቦት ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ.ም. በሚሚዮግራፍ (በእጅ ፡ ማተሚያ) ፡ ታትመው ፡ አምስት ፡ ቮሊዩም (አምስት ፡ ትልልቅ ፡ መጽሐፎች) ፡ ሆነዋል ። በነዚህ ፡ ቮሊዩም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ከተቋቋመበት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፳፱ኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ የወጡትና ፡ ያልተሻሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ በልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ከወጡት ፡ ሕጎች (ኮዶች) ፡ በቀር (ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግና ፡ የንግድ ፡ ሕግ) ፡ በሙሉ ፡ ይገኛሉ ።

---

48 (ሀ) በዝክረ ፡ ነገር ፡ መሸፈኛ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ሥዕል ፡ ደራሲው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ በቃላቸው (በአእምሯቸው ፡) ካስታወሱት ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ።

49 እንዲያውም ፡ መጽሐፉ ፡ የያዘው ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ እንደዚህ ፡ ያሉቱን ፡ አዋጆች ፡ ነው ።

50 መጽሐፉ ፡ በአንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ መግለጫዎችን (ማብራሪያዎችን ፡) የያዘ ፡ ሲሆን ፡ የቀረው ፡ ግን ፡ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ሕጎችን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

51 በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆነው ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ ከሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ስለወጡት ፡ አዋጆች ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ ኮፒ ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አዋጆች ፡ ሁሉ ፡ ታትመው ፡ እንዲወጡ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሚያስችል ፡ ውጤቱ ፡ ለሕግ ፡ አዋቆችና ፡ ለታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ያገለግላል ።

ይህም ፡ በጠቅላላው ፡ ከ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ.ም. እስከ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ የያዘ ፡ ነው ። [52]

የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ.ም. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ የሚያወጣቸው ፡ የሕግ ፡ ዐይነቶች ፡ በይበልጥ ፡ ተብራርተው ፡ ተወስነዋል ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ የሚያወጣቸውን ፡ የሚከተሉትን ፡ ሦስት ፡ ዐይነት ፡ ሕጎች ፡ ይወስናል ። [53] አዋጅ ፡ ማለት ፡ (በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በቍጥር ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ እና ፡ ፺ ፡ መሠረት) ፡ ምክር ፡ ቤት፡ ከተስማማበት ፡ በኋላ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚቀርብ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ድንጋጌ ፡ ማለት (በቍጥር ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡) አማካሪዎች ፡ ባልተሰበሰቡበት ፡ አስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ ታውጆ ፡ አማካሪዎች ፡ እንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ እንዲያጸድቁት ፡ ለአማካሪዎች ፡ የሚቀርብ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ትእዛዞች ፡ የሚባሉት ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ እንዲስማማ ፡ የማይጠየቅባቸው ፤ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በቍጥር ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ፡ ፴፯ ፡ ባላቸው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ የሚመነጩ ፡ ትእዛዞች ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ካየናቸው ፡ በአዋጅ ፡ ከሚወጡ ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ ዐይነቶች ፡ ሌላ ፡ ታውጀው ፡ የሚወጡ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሕጎችም ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚባሉና ፡ ወይም ፡ እንዲሁ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩት ፡ በየክፍላቸው ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ የሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚያወጥዋቸው ፡ ናቸው ።

በተለይ ፡ ስለሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ደግሞ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍጥር ፡ ፴ ፡ መሠረት ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎችን ፡ ለማጽደቅ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ናቸው ፤ ሆኖም ፤ የአገሩን ፡ የግዛት ፡ ክፍል ፡ የሚለውጡ ፡ ጸንቶ ፡ ያለውን ፡ የአገሩን ፡ ሕግ ፡ የሚያሻሽሉ ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ እንዲሆን ፡ የሚጠይቁ ፡ እንዲሁም ፡ ብድርና ፡ ሞኖፖልን ፡ የሚመለከቱ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ እንዲያጸድቃቸው ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። በዚሁ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ቍጥር ፡ ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆንባቸው ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ በአንድነት ፡ የአገሪቱ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ናቸው ፤ ከዚህ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ውድቅና ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ይሆናሉ ። [54]

ሕጎች (ኮዶቹ)፡ ደግሞ፡ ምንም፡ እንኳ፡ በቴክኒክ፡ ረገድ፡ ከሌሎቹ፡ ሕጎች፡ የተለየ፡ ስፍራ ፡ ባይኖራቸው ፡ ለአገሪቱ ፡ የወደፊት ፡ እድገት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚዎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በተለይ፡ ልናነሳቸው፡ ይገባል ። በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ.ም. እና ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም. መካከል ፡ ኢትዮጵያ፡ ከስድስት፡ ያላነሱ ፡ ሕጎች (ኮዶች) ፡ አውጥታለች፤ እነሱም፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ (በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ.ም. ሐምሌ ፡ ፳፫) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የንግድ ፡ ሕግና ፡ የባሕር ፡ ሕግ (በ፭ ፡ ግንቦት ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ.ም.) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት (በ፪ ፡ ኅዳር ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ.ም.) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ (በ፰ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች (ኮዶች) ፡

---

[52] <u>የተሰበሰበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ፩ ፡ ቮሊዩም</u> ፡ (አዲስ ፡ አበባ፡ ፲፱፻፷፬—፲፱፻፷፮) ፡ በተለይም፡ በቮሊዩም ፡ ፩ ፡ መግቢያውን ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ።

[53] የ፲፱፻፵፰ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በ ፡ <u>የተሰበሰበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ</u> ውስጥ ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ እስከ ፡ ፻፲፫ ፡ ተመልከት ።

[54] ያው ፡ ከገጽ ፡ ፺፮ ፡ እስከ ፡ ፻፲፪ ።

አወጣጥ ፡ ታሪክ ፡ ገና ፡ አልተጻፈም ፤ ሆኖም ፤ ከኮዶቹ ፡ አዘጋጆች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ስለ ፡ ኮዶቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምንጮች ፡ ለመምሪያ ፡ ያህል ፡ ተናግረዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለሚከተሉት ፡ ጉዳዮች ፡ እኛም ፡ ደፍረን ፡ መናገር ፡ እንችላለን ፤ በመጀ መሪያ ፡ ነገር ፡ በማዘጋጀቱ ፡ በኩል ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ድካም ፡ በኮዶቹ ፡ ውስጥ ፡ ጎልቶ ፡ ይታያል ፤ ሁለተኛ ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዎን (ለሕግ ፡ አውጭ ፡ ኮሚሲ ዎን) ፡ መነሻ ፡ የሆኑትን ፡ የኮዶች ፡ ረቂቅ ፡ ያቀረቡትና ፡ በኮዶቹም ፡ ዝግጅት ፡ ጊዜ ፡ ያማከሩት ፡ ሊቃውንት ፡ እንደ ፡ ረኔ ፡ ዳቪድ ፡ ጂ ፡ ኤስካራ ፡ ዣን ፡ ግራቨንና ፡ አ ፡ ጆፍሬ ፡ ያሉት ፡ ስማቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።[55]

የዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አራተኛ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴ ፡ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃ ፡ ሆና ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የተባለውን ፡ ሕግ ፡ የሚወጣበት ፡ ኦፊሴል ፡ ጋዜጣ ፡ ማቋቋማቸው ፡ ነው ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣው ፡ ሳያቋርጥ ፡ ታትሟል ፤ ይኸው ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣው ፡ የተቋቋመ በት ፡ የ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ.ም. ቍጥር ፡ ፩ ፡ አዋጅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚታወጁት ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ይወጡበታል ፡ ይላል ።[56] ነጋሪት ፡ ጋዜጣው ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ይታተማል ።

የሚወጣው ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ከመታተሙና ፡ ከመሰብሰቡ ፡ በላይ ፡ መንግሥት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ካወጣው ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ በተለይ ፡ አዋጆ ችን ፡ ብቻ ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ.ም. በአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ማውጣት ፡ ጀመረ ።[57] የመጀ መሪያው ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፻፲፬ ፡ ያሉትን ፡ ከ፲፱፻፴፬ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵ ፡ የወጡትን ፡ አዋጆች ፡ ይዝዋል ።

ይህ ፡ ዘመን ፡ ካለፉት ፡ ዘመናት ፡ የሚለይበት ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ የሚወ ጡት ፡ ሕጎች ፡ የሚታተሙበት ፡ ቋንቋ ፡ መለወጥ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በቍጥር ፡ ፻፳፭ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦፊሴል ፡ ቋንቋ ፡ አማርኛ ፡ ነው ፡ ቢልም ፡ ከነፃነት ፡ ወዲህ ፡ ጀምሮ ፡ ሕጉን ፡ ሁሉ ፡ በነጋ ሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ማሳተም ፡ ተለምደዋል ። ሆኖም ፡ ከዚያ ን ፡ በፊት ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ሁለተኛ ፡ የኦፊሴል ፡ ቋንቋ ፡ እንዳልተባለ ፡ ሁሉ ፡ እን ግሊዝኛም ፡ በኦፊሴል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁለተኛ ፡ ቋንቋ ፡ አልተባለም ። አሁን ፡ በቅ ርቡ ፡ ከወጡት ፡ አንዳንዶቹ ፡ ኮዶች (እነሱም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ የንግድ ፡ ሕግ) ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ረቂቆች ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ባይጻፉ ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ የቋንቋ ፡ ጉዳይ ፡ ባላነሳነው ፡ ነበር ።

---

55 በውጭ ፡ ታሪካቸው ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ ኮዶች ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የ፲፱፻፶፩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ የጃን ፡ ግራቨን ፡ ጥናት ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፴፯ ፡ በተጠቀሰው ፤ በሉንስታይን ፡ ከገጽ ፡ ፳፯ ፡ እስከ ፡ ፳፰ ፤ እንዲሁም ፡ የረኔ ፡ ዳቪድን ፡ ጽሑፎች ፡ "ሌ ፡ ሱርስ ፡ ዱ ፡ ኮድ ፡ ሲቢል ፡ ኢትዮፒየን ፡ "በ ፡ ሬቩ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ድሯ ፡ ኮምፓሬ (፲፱፻፷፪ ፡) ከገጽ ፡ ፬፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ፭፻፮ ፡ "ሲቢል ፡ ኮድ ፡ ፎር ፡ ኢትዮጵያ" ፡ በ ፡ ቱሌን ፡ ሎ ፡ ረቢው ፡ (፲፱፻፷፫ ፡) ከገጽ ፡ ፻፹፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፬ ፡ እና ፡ "ስትረክቱር ፡ ኤ ፡ ኦሪጂናሊቴ ፡ ዱ ፡ ኮድ ፡ ሲቢል ፡ ኢቲዮፒየን" ፡ በዛይትሽሪፍት ፡ ፋር ፡ አውስላንዲሺስ ፡ ኡንድ ፡ ኢንተርናሺዮናሊሽስ ፡ ፕሪቫትሬሀት ፡ (፲፱፻፷፭ ፡) ከገጽ ፡ ፮፻፷፷ ፡ እስከ ፡ ፮፻፹፩ ፡ ተመልከት ።

56 የተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ከገጽ ፡ ፻፶፬ ፡ እስከ ፡ ፻፷ ፡ ተመልከት ።

57 የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አዋጆች ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፭ ፡) ተመልከት ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በተለይ ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች (ልዩ ፡ መብቶችን ፡ የሚሰጡ ፡ ሕጎች ፡ ኮንሴሲዮኖችና ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች) ፡ ሳያቋርጡ ፡ ተሻሽለዋል ።

ሆኖም ፤ ልዩ ፡ መብት ፡ የሚሰጡ ፡ ሕጎች ፡ ለየት ፡ ያሉ ፡ ፎርሞች ፡ ተከትለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚከተሉት ፡ ፎርም ፡ ቢለያይም ፡ "ቻርተር" ፡ የሚባል ፡ የወል፡ ስም ፡ ተሰጥቷቸዋል ። ስለዚህ ፡ ለብዙ ፡ ድርጅቶች ፡ ተራ ፡ ቻርተር (ለምሳሌ ፡ ለነጋዶች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ስፖርት ፡ ፌዴሬሽን) ፡ ወይም ፡ በትእዛዝ (ለምሳሌ ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ለመንበረ ፡ ጸባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ ለወጣቶች ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር) ፡ ቻርተሮች ተሰጥተዋል ። [58] የኤኮኖሚ ፡ ጉዳይ ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ ግን (ለምሳሌ ፡ የማዕድን ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ የባቡር ፡ ሀዲድ ፡ ኮንሴሲዮኖች) ፡ ታትመው ፡ የሚወጡ ፡ ስለማይመስል ፡ ዛሬ ፡ በአዋጅ ፡ ከሚወጣው ፡ ሕግ ውስጥ ፡ ያላቸውን ፡ ስፍራ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም ።

ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደገለጽነው ፡ ደግሞ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ (ትሪቲዎች) ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍጥር ፡ ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የአገሪቱ ፡ የበላይ ፡ ሕጎች ፡ ስለተባሉ ፡ በአዋጅ ፡ በሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ መካከል ፡ ከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ተሰጥቷቸዋል ። [59] የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች (ትሪቲዎች) ፡ የሚባሉት ፡ በሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ቻርተር ፡ የአፊሪካ ፡ አንድነት ፡ ቻርተር ፡ ያሉትም ፡ ናቸው ። ኢትዮጵያ ፡ በአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ የፈጸመችው ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባርና ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎችንም ፡ በሕገ ፡ መንግሥትዋ ፡ ቍጥር፡ ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ የበላይነት ፡ ያላቸው ፡ ሕጎች ፡ ማድረግዋ ፡ አገሪቱ ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉቱ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ እምነት ፡ ያላት ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል ። [60]

አሁን በቅርቡ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ አጠቃልለው ፡ ያወጡት ፡ መጻሕፍት ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎችን (ትሪቲዎችን) ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ አለመመዝገባቸው ፡ ያሳዝናል ። ከአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተርና ፡ ከአሥራ ፡ አራት ፡ የተወሰኑ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ጉዳዮችን ፡ ከሚመለከቱ (አብዛኞቹ፡ የክሬዲት ፡ ወይም ፡ የብድር ፡ ውሎች) ፡ በስተቀር ሌሎች ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ አልተመዘገቡም ። [61] ያልተመዘገቡበትም ፡ ምክንያት ፡ እነዚህ ፡ የሕግ ፡ ማጠቃለያ ፡ መጽሐፎች ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሰበስቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲጸድቁ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ የማይቀርቡ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ (ትሪቲዎች) ፡ በነጋሪት ጋዜጣ ፡ አይወጡም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ በነ

58 የተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ ቮሊዩም ፡ ፳ ፡ ከገጽ ፡ ፻፴፯ ፡ እስከ ፡ ፻፺፰ ፡ ተመልከት ።

59 ያው ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ገጽ ፡ ፻፲፪ ።

60 በተሰበሰበው ፡ ሕግ ፡ በቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተር ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቀጥሎ ፡ ከማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ቀድሞ ፡ መጻፍም ፡ ይህንኑ ፡ ያሳያል ።

61 ያው ፤ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ቮሊዩም ፡ ፪ ፡ ከገጽ ፡ ፴፯ ፡ እስከ ፡ ፶፩ ፡ ተመልከት ።

ጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የማይወጡትን ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ለማወቅ ፡ ቢሻ ፡ ከደንበኞቹ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ውጭ ፡ መፈለግ ፡ አለበት ።[62]

ከ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በአዋጅ ፡ ስለወጡት ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ በተደረገው ፡ በዚህ ፡ አጭር ፡ ምርመራ ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ሕጎች ፡ ይልቅ ፡ በቅርቡ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ምንጭ (ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ዶኩማዎች) ፡ ማግኘት ፡ የሚቀል ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ያበረከቱት ፡ ሁሉ ፡ ታውቆ ፡ አስተያየት ፡ እንዲሰጥበት ፡ ለማድረግ ፡ ታሪክ ፡ ለሚያፈቅሩ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ሰፊ ፡ የጥናት ፡ በር ፡ ገና ፡ ክፍቱን ፡ ነው ።

፪ ፤ ልማድ ፤

ምንም ፡ እንኳ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ልማድ ፡ ዋናው ፡ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ ቢሆንም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በደንብ ፡ ባለመጠናቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ የሕግ ፡ ምንጭነት ፡ የምንናገረው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደሚታየው ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ጉዳይ ፡ በኤርትራና ፡ በቀረው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ የተለየ ፡ ሁናቴ ፡ መኖሩ ፡ ሊታወቅ ፡ ይገባል ። እስኪ ፡ አስቀድመን ፡ ልማድ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ እንወስንና ፡ ስለ ፡ ልማድም ፡ የሕግ ፡ ምንጭነት ፡ ዋናቹን ፡ ችግሮች ፡ እንመልከት ።

ልማድ ፡ ማለት ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የሚቆጥራቸውና ፡ የሚያስከብራቸው ፡ አንዳንድ ፡ ሁናቴዎች ፡ ናቸው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ለልማድ ፡ የሰጠነው ፡ ትርጉም ፡ ራሱ ፡ ልማድ ፡ ያልተጻፉ ፡ ሕዝብ ፡ የተቀበላቸውና ፡ የሚከተላቸው ፡ የአንዳንድ ፡ አድራጎት ፡ ሁናቴዎች ፡ ውጤት ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ልማድ ፡ ባለመጻፉ ፡ የልማዱን ፡ ሕግ ፡ የሚያከብረው ፡ ሕዝብ ፡ አባል ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ልማዱን ፡ ማወቅ ፡ ያስቸግረዋል ። ልማዱን ፡ የሚያከብረው ፡ ሕዝብ ፡ አባሎች ፡ ግን ፡ ልማዱ ፡ ከዕለት ፡ አድራጎታቸው ፡ ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ በትምህርትም ፡ ከሚሰጣቸው ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ አንዱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያውቁታል ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ በአንዳንድ ፡ አጋጣሚ (የውጭ) ፡ ምክንያቶች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ልማድ ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ ሊታወቅ ፡ አይችልም ። አጋጣሚውም ፡ ምክንያት ፡ መንግሥት ፡ ልማዱን ፡ ማወቅ ፡ ሲፈልግ (ልማዱን ፡ ለመቆጣጠርና ፡ ዳኝነትን ፡ ለማስተካከል) ፡ ወይም ፡ ሊቃውንት (ያልታወቀን ፡ ነገር ፡ ለማወቅና ፡ ለመረዳት ፡ በጥበብና ፡ በዕውቀት ፡ ፍቅር ፡ ተገፋፍተው) ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። መንግሥት ፡ ልማድን ፡ ለማጥናት ፡ የሚወስደው ፡ እርምጃ ፡ ለልማድ ፡ ሕግ ፡ ደንበኛ ፡ አቋም ፡ ሰጥቶ ፡ በአዋጅ ፡ እንዲወጣ ፡ ለማድረግ ፡ ያስችላል ፤ ለምሳሌ ፡ ከ፲፰ኛውና ፡ ከ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመቶች ፡ ጀምሮ ፡ የፈረንሳይና ፡ የቤልጅግ ፡ አገሮች ፡ የፈረንሳይ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ የነበሩት ፡ የምዕራብ ፡ አፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ ከ፲፱፻፷ ፡ ዓ.ም. በኋላ ፡ ፓንጃብ ፡ በ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የዳች ፡ ምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ በ፲፱ኛውና ፡ በ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እንዳደረጉት ።[63]

---

62 ለምሳሌ ፡ ለአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ሕዝቦች ፡ ዛሬም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚሰጡት ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ወርቃዊ ፡ አዋጆች (ጎልደን ፡ ኤዲክትስ ፡) የሚባሉ ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ በተራ ፡ ጋዜጣ ፡ እንጂ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አይወጡም ።

63 ስለነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እርምጃዎች ፡ ጂ ፡ ጊልሴን ፡ ላ ፡ ሬዳክሲዎ ፡ ዴ ፡ ኩቱም ፡ ዳ ፡ ለ ፡ ፓቤ ፡ ኤ ፡ ለ ፡ ፕሬዛ ፡ (ብሩክሲል ፡ ፲፱፻፸፪ ፡) ተመልከት ።

ሁለተኛው ፡ ዐይነት ፡ ግን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በምርምርና ፡ ልማዱን ፡ በቅርቡ ፡ በማጥናት ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ። (ለምሳሌ ፡ የእንግሊዝና ፡ የአሜሪካ ፡ ሊቃውንት ፡ በሶሻል ፡ አንትሮፖሎጂ (የሰውን ፡ ጠባይ ፡ በኅብረተ ፡ ሰብ) ፡ ባደረጉት ፡ ጥናት ፡ ስለ ፡ አፍሪካ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ያበረከቱትን ፡ በጥናቱ ፡ በጣም ፡ ከተራቀቁት ፡ ቦህናን ፡ ግለክማንና ፡ ስካፓራን ፡ እንጠቅሳለን) ። ሆኖም ፤ ልማድን ፡ መንግሥት ፡ በሚመዘግብበት ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ የሚሰጣቸው ፡ የልማዱ ፡ ሕግ ፡ የራሳቸው ፡ በመሆኑ ፡ የልማዱ ፡ ሕግ ፡ ለተዋሀዳቸውና ፡ አረጋግጠው ፡ ለሚያውቁት ፡ ሰዎች ፡ ነው ፤ (እርግጥ ፡ ነው ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ልማዱን ፡ ለሌሎች ፡ መናገር ፡ ቢችሉ ፡ የተዋሀዳቸውን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አውጥተው ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ መቅረጽ ፡ ስለሚቸግራቸው ፡ ርዳታ ፡ ያስፈልጋቸዋል ።) ሊቃውንቱ ፡ የሆኑ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ልማዱን ፡ በሚያጠኑበት ፡ ቦታ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ቢቆዩ ፡ ሁልጊዜ ፡ የውጭ ፡ ተመልካቾች ፡ ናቸው ። በመጀመሪያው ፡ ዐይነት ፡ ከሚሠራው ፡ የሚገኘው ፡ ውጤት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝቡ ፡ አባሎች ፡ ስለልማዱ ፡ የሚሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ፡ ያልተጣራና ፡ ያልተሟላ ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ለልማዱ ፡ የውጭ ፡ ተመልካች ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የሚያቀርበው ፡ ግልጽ ፡ ያለና ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ከሚታየው ፡ የሰዎች ፡ አድራጎት ፡ ውስጥ ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ያለውን ፡ ሁናቴ ፡ ላይደርስበት ፡ ይችላል ። [64]

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ካለንበት ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በደንብ ፡ አለመታወቁ ፡ የታመነ ፡ ነው ። አገር ፡ ጎብኝዎች ፡ ከጸፉት ፡ (እነዚህም ፡ እምነት ፡ የሚጣልባቸው ፡ ምንጮች ፡ አይደሉም ፤ ምክንያቱም ፡ መንገደኞቹ ፡ የልማዱ ፡ ባለቤት ፡ የሆነው ፡ ሕዝብ ፡ ወገኖች ፡ ባለመሆናቸው ፡ ወይም ፡ ለዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ ሥራ ፡ በሳይንስ ፡ ረገድ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሊቃውንት ፡ ባለመሆናቸው ፡ ነው ፤) አንዳንድ ፡ የሶሻል ፡ አንትሮፖሎጂ ፡ ጽሑፎች ፡ [65] በቀር ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑት ፡ ዶኩማዎች ፡ የተጻፉ ፡ ኤርትራ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ በነበረች ፡ ጊዜ (ስለ ፡ ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ) ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኮሎኒያል ፡ ቀንበር ፡ ስር ፡ በነበረች ፡ ጊዜ (አብዛኞቹ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉት ፡ የታተሙ ፡ በ፲፱፻፴፯ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ [66] ዓ.ም. መካከል ፡ ነው) በኢጣሊያን ፡ ሊቆች ፡ ነው ። ዘመናዊ ፡ ኢንስቲቱሲዮኖች ፡ እየተተከሉ ፡ ሲሄዱ ፡ ልማድ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ስለሚጠፋ · በሕግ ፡ ሳይንስና ፡ በይበልጡም ፡ ደግሞ ፡ በሕግ ፡ ታሪክ ፡ በኩል ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ አለመታወቅ ፡ ሊጠገን ፡ የማይችል ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርስ ፡ ይችላል ። ዶክቶር ፡ ዳ ፡

64 በመጨረሻ ፡ የተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ተሰጥዎች ፡ በተለይ ፡ ያሏቸውን ፡ እላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሊቃውንት ፡ አይመለከትም ።

65 አልቫሬዝ ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስላደረገው ፡ ጉዞ፡ በጻፈው፡ ውስጥ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ብዙ ፡ መግለጫዎች ፡ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፡ ከገጽ ፡ ፺፫ ፡ እስከ ፡ ፺፭ ፡ ከ፻፩ ፡ እስከ ፡ ፻፫ ፡ ፻፳፫ ፡ ፪፻፴፯ ፡ ፪፻፸፫ ፡ በ ፡ ዘ ፡ ፕሬስተር ፡ ጆን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኢንዲስ ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ (ለንደን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡) ተመልከት ።

66 የካፖማዛን ፡ የኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የፔታዚ ፡ የፖሌራና ፡ የሮዶንን ፡ ጥናቶች ፤ እንዲሁም ፡ አዘጋጃቸው ፡ ያልታወቀውን ፡ በዚያኑ ፡ ዘመን ፡ በትግርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የታተሙትን ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ በተጠቀሱት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፤ እነዚህም ፡ በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ በልማድ ፡ ክፍል ፡ (ሁለተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተሰጥተዋል ፤ ተመልከት ።

ማርዳ ፡ የተባሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ጠቃሚ ነት ፡ በቅርቡ ፡ በጻፉት ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በመደገፍ ፡ ጥሩ ፡ አድርገው ፡ ኢትተዋል ። [67]

ስለ ፡ ኤርትራ ፡ ካሉት ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነው ፡ የኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ መጽሐፍ ፤ ፕሪንቺፒ ፡ ዲ ፡ ዲሪቶ ፡ ኮንሱኤቱዲናሪዎ ፡ ዴል ፡ ኤሪትሬያ ፡ የተባለው ፡ አስቀድሞ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይገባል ፤ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያረጀም ፡ ቢሆን (በ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ.ም. ነው ፡ የታተመ) ፡ ዛሬም ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ለሚደረገው ፡ ጥናት ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ መነሻ ፡ ነው ። [68] ሁለተኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ደግሞ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደጠቀስነው ፡ ያለው ፡ መንግሥት ፡ የሰበሰበው ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ የተሰበሰበውን ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ በማርቀቅ ፡ ከሕዝቡም ፡ ውስጥ ፡ የተማሩት ፡ ተካፋይ ፡ ሆነዋል ። የመጀመሪያዎቹ ፡ ክፍሎች ፡ የተረቀቁት ፡ በዚህ ፡ መቶኛ ፡ ዓመት ፡ [69] በመጀመሪያዎቹ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለሰላሳ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ካቋረጠ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ የተጠኑ ፡ ወጡ ። [70]

በሌላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ግን ፡ ጣሊያኖች ፡ አገሪቱን ፡ በያዙበት ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ አጥንተዋል ። [71] ከነጻነት ፡ በኋላ ፡ አንዳንድ ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፎች ፡ በጣሊያን ፡ በእንግሊዝና ፡ በአሜሪካን ፡ አንትሮፖሎጂስቶች ፡ ተጽፈዋል ። [72] ሆኖም ፤ እነዚህ ፡ የተደከመባቸው ፡ ጥናቶች ፡ በየስፍራው ፡ ተበታትነው ፡ ስለሚገኙ ፡ በ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ.ም. ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ስለ ፡ ኤርትራ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ ያለ ፡ አጠናቅሮ ፡ በማዋሀድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ባህል ፡ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ከሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ጠቅላላ ፡ መግለጫ ፡ ለመስጠት ፡ የተሞከረ ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ዎከር ፡ ባሳተመው ፡ መጽሐፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [73]

ሆኖም ፤ በደራሲው ፡ አስተያየት ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በይበልጥ ፡ ሊያበረክቱ ፡ የሚችሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ልማድ ፡ አንዳንድ ፡ አልፎው ፡ አልፎው ፡ የተደረጉ ፡ ጥናቶች ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የኤትኖሎጂ (ነገረ ፡ ሰብ) ፡ ማኅበር ፡ መጽሔት ፡ ታትመዋል ። [74] የሚያሳዝነው ፡ እነዚህ ፡ ጥና

---

67 "ኖሎሬ ፡ ጁሪዲኮ ፡ ዴሌ ፡ ኮንሱዌቱዲኒ ፡ ኤቲዮፒኬ ፡" በ ፡ አቲ ፡ ዴል ፡ ኮንቤኞ ፡ ኢንተርናሲዎናሌ ፡ ዲ ፡ ሱዲ ፡ ኤቲዮፒቺ ፡ (ሮማ ፡ ፲፱፻፰ ፡) ከገጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፳፪ ፡ ተመልከት ።

68 ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ፕሪንቺፒ ፡ ዲ ፡ ዲሪቶ ፡ ኮንሱኤቱዲናሪዎ ፡ ዴል ፡ ኤሪትሬያ ፡ (ሮማ ፡ ፲፱፻፲፮) ።

69 በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፮ ፡ ተመልከት ።

70 የአስቲኒን ፡ የሆፍነርን ፡ የኮንቲ ፡ ሮሲኒንና ፡ የፋዚላን ፡ ጥናቶች ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፮ ፡ በተጠቀሱት ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ በልማድ ፡ ክፍል ፡ (ሁለተኛ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

71 ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ብሮቶና ፡ ሌሎችም ፡ ያጠኑትን ፡ በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ በልማድ ፡ ክፍል ፡ (ሦስተኛ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ፤ እንደዚሁም ፡ ዘ ፡ ፐብሊኬሽንስ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፕሪንሲቶን ፡ ኤክስፔዲሽን ፡ ቱ ፡ አቢሲኒያ ፡ በ ፡ ኢ ፡ ሊትማን ፡ ቮሊዩም ፡ ፱ ፡ ከገጽ ፡ ፻፩ ። ቍጥር ፡ ፲፮ ፡ በተጠቀሱት ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ።

72 ቸሩሊ ፡ ሀንቲንግፎ ፡ ሌቪን ፡ ሚሲን ፡ ሻክና ፡ ሌሎችም ፡ ያጠኑትን ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በልማድ ፡ ክፍል ፡ (በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ። በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፮ ፡ እንደተጠቀሰው ።

73 ሲ ፡ ኤች ፡ ዎከር ፡ ዘ ፡ አቢሲኒያን ፡ አት ፡ ሆም ፡ (ለንደን ፡ ፲፱፻፴፫) ።

74 ለምሳሌ ፡ በ ፡ ዘ ፡ ቡሌቲን ፡ ኦፍ ፡ ኢትኖሎጂካል ፡ ሶሳየቲ ፡ ከተጠቀሱት ፡ በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ከተጠቀሱት ፡ በልማድ ፡ ክፍል ፡ (በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

ቶች ፡ በደንብ ፡ ስላልታወቁ ፡ የተጠቀመባቸው ፡ የለም ። ስለ ፡ ልማድ ፡ የተዘጋጁ ፡ ያልታተሙ ፡ ጽሑፎችም ፡ በአንዳንድ ፡ የግል ፡ ሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ቤት ፡ ይኸው ፡ ዕድል ፡ ገጥሟቸዋል ። ብዙ ፡ የተማሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይህን ፡ የአገራቸውን ፡ የባህል ፡ ቅርስ ፡ ሳይጠፉ ፡ መመዝገብ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑ ፡ ይሰማቸዋል ። በግል ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ከሚገኙት ፡ ጥናቶች ፡ ከምንጩ ፡ በመጠየቅ ፡ የተሰበሰቡ ፡ በደራሲው ፡ ዘመዶችና ፡ ወዳጆችም ፡ ዘንድ ፡ ጭምር ፡ የሚገኙ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ታትመው ፡ ስለማያውቁ ፡ ሊቃውንትና ፡ ሌሎች ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እነዚህን ፡ ከፍተኛ ፡ ጽሑፎች ፡ ሊያገኙ ፡ አልቻሉም ። እነዚህ ፡ ጽሑፎች ፡ ከየተደበቁበት ፡ እንደሚወጡ ፡ ተስፋችን ፡ ትልቅ ፡ ነው ። የሚፈልጓቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲያገኙዋቸው ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ጉዳይ ፡ ያሏቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማኖር ፡ በደስታ ፡ የፈቀዱትን ፡ የባላንበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀልን ፡ ምሳሌ ፡ ብዙ ፡ ደራሲዎች ፡ እንደሚከተሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።[75]

እላይ ፡ ካየናቸው ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ከተጻፉት ፡ ደንበኛ ፡ መግለጫዎች ፡ በቀር ፡ ልማድ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ በታወቀና ፡ በተራ ፡ አቀራረብ ፡ በምሳሌም ፡ ይጻፋል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አውሮፓውያን ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ ሕዝቡ ፡ ሕጉን ፡ የሚገልጥበትን ፡ ፈሊጥ ፡ ቢያኳስሱ ፡ አንትሮፖሎጂስቶች ፡ ሕግን ፡ በዚህ ፡ ባልተለመደ ፡ መንገድ ፡ መጻፍ ፡ ይወዳሉ ። ከነዚህ ፡ ምሳሌዎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ተሰብስበው ፡ ያባቶች ፡ ቅርስ ፡[76] በሚል ፡ ስያሜ ፡ በባላንበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ በአማርኛ ፡ መታተማቸው ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። ደራሲው ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ የሚጠጉ ፡ ምሳሌዎች ፡ ከመሰብሰባቸው ፡ በላይ ፡ ብዙዎቹ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ጉዳይ ፡ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ በመግቢያው ፡ ይናገራሉ ።[77] ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ አጫጭር ፡ ምሳሌዎች ፡ በደንብ ፡ ቢተረጐሙ ፡ እንኳ ፡ ኖሮ ፡ እንኳን ፡ ከውጭ ፡ ለመጣ ፡ ሕግ ፡ አዋቂና ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ወጣቶችም ፡ ግልጽ ፡ አይሆኑም ። አንባቢ ፡ ትርጉማቸውን ፡ እንዲረዳና ፡ ጥቅማቸውን ፡ እንዲያውቅ ፡ እያንዳንዱ ፡ ምሳሌ ፡ በሕግነቱ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትርጉም ፡ የሚያብራሩ ፡ ነ ጭር ፡ ቃላት ፡ ያስፈልጉታል ። ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ባላንበራስ ፡ የልማድ ፡ ሕግን ፡ ለማጥናት ፡ የሚፈልጉ ፡ ሕግ ፡ አዋቆች ፡ ካሉ ፡ ልማዱን ፡ አሟልተው ፡ እንዲያውቁ ፡ ከሚረዷቸው ፡ ሰዎች ፡ አገናኛቸዋለሁ ፡ ሲሉ ፡ ቃል ፡ ገብተዋል ።

በዚህ ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ እንደ ፡ ተረዳነው ፡ በአዋጅ ፡ ስለወጣ ፡ ሕግ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ሕግም ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ ያስፈልጋል ።

አንዳንዶቹ ፡ የልማድ ፡ ሕጎች ፡ በተለይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዛሬም ፡ ስለሚሠራባቸው ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ጥናቱ ፡ በይበልጥ ፡ ያስፈልጋል ፤ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ በአዋጅ ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ ግን ፡ ነ ብዛኞቹ ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ሆነዋል ። በ፲፱፻፳ ፡ ዓ.ም. የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎችን ፡ በሚሽረው ፡ ክፍሉ ፡ የልማድ ፡ ሕጎችን ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሻራቸው ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ተጫናቸው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡

---

75 እነዚህ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ ቡልጋ ፡ ክፍለ ፡ አገር (የሕግና ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ስለሆኑ ፡) ልማዶች ፡ ጥናት ፡ ይዘዋል ፡ (የአርሺብ ፡ ካታሎግ ፡ ኤስ ፡ ፷፱) ።

76 አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፪ ።

77 ያው ፡ ከገጽ ፡ ፮ ፡ እስከ ፡ ፯ ።

በቅርቡ ፡ በጻፉት ፡ [78] ተችተዋል ። የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፶፯ (፩) መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ያለው ፡ የሕግነት ፡ ኃይል ፡ እስከምን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰጡት ፡ በአብዛኛው ፡ አሳብ ፡ እስማማ ለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡ የልማድ ፡ መግቢያ ፡ በሮች ፡ የሚል ዋቸው ፡ አንድም ፡ በኮዱ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ በተለይ ፡ የተጠቀሱትን (እርሳቸውም ፡ ከተጠቀሱት ፡ ውስጥ ፡ ዘርዝረዋል) ፤ ወይም ፡ ሕግ ፡ ለማይገኝለት ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ልማድን ፡ መተካት ፡ ስለሚቻልበት ፡ ሁናቴ (ለዚህም ፡ የጠቀሱት ፡ ምሳሌ ፡ ዕቁብ ፡ ጥሩ ፡ ነው) ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ለሕግ ፡ በሚሰጡት ፡ ትርጉም ፡ ልማድን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የሚያደርጉበት ፤ በመጨረሻም ፡ ጸሐፊው ፡ ከሕግ ፡ በላይ (ፓራ ፡ ሊጋል) ፡ የሚሉት (ማለት ፡ ሕጉ ፡ ልማዱን ፡ ለይቶ ፡ ባይጠቅስም ፡ እንኳ ፡ ባህላዊ ፡ ድርጅቶች ፡ ቅድሚያ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ሲያደርግ ፡ ልማዱ ፡ እንዲሠራ በት ፡ ሥልጣን ፡ ከመስጠት ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ለምሳሌ ፡ በጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ አገልግሎት) ፡ ናቸው ። ሆኖም ፤ ጸሐፊው ፡ የጥናታቸውን ፡ ውጤት ፡ በመደምደሚያው ፡ ሲሰጡ ፡ ሕጎችን ፡ የሚሽ ረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፡ በሕግነት ፡ ሊያገለ ግል ፡ የሚችልበትን ፡ ክፍል ፡ በጣም ፡ ያጠበዋል ፡ በማለታቸው ፡ የተሳሳቱና ፡ ከትክክለኛው ፡ ሁናቴ ፡ የራቁ ፡ ይመስለኛል ። [79] በተለይም ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በይ በልጥም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ሕግ ፡ ዛሬ ፡ በአፍሪካ ፡ ያለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ የተመለ ከትን ፡ እንደሆነ ፡ ስሕተቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፷፯ (፪) መሠረት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ሊያገባ ፡ ይችላል ፤ ጋብቻ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑ ፡ የሚታየው ፡ በከፊል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባሉት ፡ ቋሚ ፡ ድንጋጌ ዎች ፡ ነው ፤ በከፊልም ፡ ለጉዳዩ ፡ ተፈጻሚ ፡ በማሆነው ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ (ምንም ፡ እንኳ ፡ ምክንያቱ ፡ ካሣ ፡ ሊያስከፍል ፡ ቢችል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፹ ፡ ፮፻፮ ፡ ፮፻፴፫ ፡ እና ፡ ፮፻፴፬ ፡ መሠረት ፡ በልማድ ፡ ምክንያቶች ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።) ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፯ ፡ መሠረት ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በጋብቻ ፡ ውል ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ የየራሳቸው ፡ የግል ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ሱብአዊ ፡ ግንኙነታቸውም ፡ ሳይ ቀር ፡ ጉዳዩም ፡ መሠረታዊ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል (ከሰብአዊ ፡ ግንኙነቶች ፡ ውል ፡ እንዳይደረግባቸው ፡ የተከለከሉት ፡ ስለ ፡ መከባበር ፡ መረዳዳትና ፡ መተጋገዝ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፮ ፡ የተጻፉት ፡ ብቻ ፡ ይመስላሉ) ፤ እንዲስማሙ ፡ ይፈቅድላቸዋል ። በመጨረሻም ፡ ጋብቻው ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚቀርቡ ፡ የመፋታት ፡ ብይን ፡ ለመስጠት ፡ ጭምር ፡ ሥልጣን ፡ ላላቸው ፡ ለነ ዚሁ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ለፍቺው ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ኮዱ ፡ የተወ ሰኑ ፡ ሁናቴዎች ፡ ቢያደርግ ፡ ሽማግሎቹ ፡ ስለማፋታት ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሰፊ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ተጋቢዎቹ ፡ ከፈለጉ ፡ ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ ከጋብቻ ፡ ጉዳዮች ፡ ብዙ ዎቹ ፡ በልማድ ፡ ሕግ ፡ ስር ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

ሆኖም ፤ ፕሮፌሰር ፡ ክሸችኖቪች ፡ ስለ ፡ ሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ዋና ፡ መቃወ ሚያ ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ በኮዱ ፡ ፳፩ኛው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፫ሺ ፫፻፶፰ ፡ የተሰ

78 "ኤ ፡ ኒው ፡ ሎጂስላቲቭ ፡ አፕሮች ፡ ቱ ፡ ከስተማሪ ፡ ሎ ፡ ዘ ፡ 'ሪፒልስ ፡' ፕሮቪዠን ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ አፍ ፡ ፲፱፻፷ ፡" በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ መጽሔት ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፶፯ ፡ እስከ ፡ ፷፯ ።

79 ያው ፡ ገጽ ፡ ፷፭ ።

ጠውን ፡ ከፍተኛ ፡ ድንጋጌ ፡ ችላ ፡ ብለው (አቃልለው) ፡ ማለፋቸው ፡ ነው ። የቍጥሩ ፡ ቃል ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

"(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ለማስገኘት ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ የሚጠይቃቸው ፡ አቋሞች ፡ ከዱሮው ፡ የተለዩ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፤ በተሻረው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩት ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፪) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ በተሻረው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩት ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያስገኙዋቸውን ፡ ውጤቶች ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ አይለውጣቸውም ።"

ይህ ፡ ቍጥር ፡ ኮዱ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ ሕጋዊ ፡ ሁናቴዎች ፡ ሁሉ ፡ <u>የቀድሞው ፡ እንደ ፡ ነበር</u> (ስታተስ ፡ ኮ ፡ አንቴ) ፡ የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ያከብራል ፤ ይህም ፡ ማለት ፡ ከመስከረም ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ የጸኑ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የቍጥር ፡ ፫ሺ ፫፻፵፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ኮዱ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ከተፈጠሩት ፡ ሕጋዊ ፡ ሁናቴዎች ፡ የሚነሱት ፡ ጉዳዮች ፡ በኮዱ ፡ የሚመሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል ፤ ይህም (ሕጋዊ ፡ ሁናቴዎቹን ፡ ስለ ፡ ፈጠሩት ፡ ሕጎች ፡ ክርክር ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር) ፡ ልማድ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ከለከለ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ።[80] በኔ ፡ አስተያየት ፡ ስለ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ የተሰጠው ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ተቃራኒ ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አንደኛ ፡ በኮዱ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ትርጉም ፡ የሚደግፍ ፡ ነገር ፡ የለም ። ሁለተኛ ፡ ትርጉሙ ፡ ከቍጥር ፡ ፫ሺ ፫፻፵፩ ፡ ጋር ፡ አይስማማም ።

"(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ለሚወስነው ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ለሆነው ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ ለተገኙት ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ በጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ዘመኑ ፡ ያላለቀለት ፡ ውል ፡ በማታለል ፡ በኃይል ፡ ዐይነት ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈርስ ፡ ካልተጠየቀ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።"

የቍጥሩ ፡ አርዕስት ፡ እንኳ ፡ "ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡" ስለሚል ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ቃሎች ፡ የሚመለከቱ ፡ የነበሩትን ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በቍጥሩ ፡ ከውል ፡ ስለሚነሱ ፡ ሁናቴዎችና ፡ በሌሎች ፡ ሁናቴዎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ተደርጓል ። በኮዱ ፡ የተደነገጉት ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ሌሎቹ ፡ ሁናቴዎች ፡ በሚያስከትሏቸው ፡ ውጤቶች ፡ ላይ ፡ ነው ። ከውል ፡ የተገኙ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁናቴዎች ፡ ግን ፡ እነዚህም ፡ ጋብቻን ፡ ይጨምራሉ ፡[81] ውጤታ

---

[80] ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከሚገኙ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ጋር ፡ ተከራክሬበታለሁ ።

[81] በቴምሬ ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ያለው ፡ ፕሮብሌም ፡ (ጋብቻ ፡ ውል ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ኢንስቲቱሲዎን ፡) በሰፊው ፡ ለማተት ፡ ይቻላል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ለማንሳት ፡ የፈለግነው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ እና ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጋብቻ ፡ በውልነት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሁናቴ ፡ ነው ።

ቸው ፡ የሚመራው ፡ የሚታየው (በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ ከተጠቀሱት ፡ በማታለልና ፡ በኃይል ፡ ከተደረጉት ፡ ውሎች ፡ በቀር) ፡ ውሎቹ ፡ በተደረጉበት ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ከኮዱ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ አብዛኛውም ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ነው ። አዲስ ፡ የሕግ ፡ ሁናቴ ፡ ሲፈጠር ፡ ወይም ፡ ዱሮ ፡ የነበረው ፡ ሕግ ፡ ሲሻሻል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በዚያ ፡ ሁናቴ ፡ ውጤቶች ፡ ላይ ፡ ኮዱ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆን ፤ የዚህም ፡ ጠቅላላ ፡ ውጤት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኮዱ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጠሩ ፡ ብዙዎች ፡ ሕጋዊ ፡ ሁናቴዎች ፡ አሉ ፤ የነዚህ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁናቴዎች ፡ ውጤት ፡ ሁናቴው ፡ እንዲለወጥ ፡ እስከ ፡ ተደረገ ፡ ድረስ ፡ የሚመራው ፡ በልማድ ፡ ሕግ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሰጠነው ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛ ፡ ከሆነ ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ የሚሠራበት ፡ ክፍል ፡ እንደሚታሰበው ፡ ሳይሆን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ የልማድን ፡ ሕግ ፡ መጠናት ፡ አስፈላጊ ፡ ከሚያደርጉት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ የሕግን ፡ ዘመናዊ ፡ እድገት ፡ የሚቃወም ፡ እንዳልሆነ ፡ ሊታወቅ ፡ ይገባል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ራሳቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ ሲያውጁ ፡ "ሕጉ ፡ ከወጣላቸው ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የሚደርስ ፡" እና ፡ "ፍላጎታቸውን ፡ ልምዳቸውን ፡ የሚጠብቅ ፡" መሆን ፡ አለበት ፡ ብለዋል ።[82] በቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ እና ፡ ፫ሺ፫፻፵፰ ፡ እንደ ፡ ተሰጡት ፡ ያሉት ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ሕጎች ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የገለጹት ፡ ዐይነት ፡ የሕዝብ ፡ ፍላጎት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስችሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ልማድ ፡ የሕግ ፡ ኃይል ፡ የሚኖረው ፡ ከሆነ ፡ ልማዱ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ፤ ለመታወቅ ፡ ደግሞ ፡ መጠናት ፡ አለበት ።

፫ ፤ ከዳኞች ፡ ፍርድ ፡ የሚገኝ ፡ ሕግ ፤

ከዳኛ ፡ ፍርድ ፡ የሚገኝ ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ከዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚመነጨው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ነው ፤ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ስንል ፡ ደግሞ ፡ እንደተለመደው ፡ የደንበኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሌሎችንም ፡ ክፍሎች ፡ ይጨምራል ። በኢትዮጵያ ፡ የዙፋን ፡ ችሎትን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድን ፡ ሥልጣን ፡ ይጨምራል ። ከዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚመነጩ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ የወል ፡ ጠባይ ፡ አንደኛ ፡ ከሙግት ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ፤ በመሠረቱ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አይደሉም ። በኢትዮጵያ ፡ ኮድ ፡ ካላቸው ፡ ከብዙ ፡ አገሮች ፡ የተለየ ፡ ሁናቴ ፡ አለ ፤ እሱም ፡ ከዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ስለሚገኝ ፡ ሕግ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ አለመኖሩ ፡ ነው ። በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በፈረንሳይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭ ፡ እንደተጻፈው ፡ ያለ ፡ አይገኝም ። የቍጥሩም ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡— "ዳኞች ፡ የሚቀርቡላቸውን ፡ ክሶች ፡ ድንጋጌ ፡ በመስጠት ፡ መልክ ፡ ሊፈርዱ ፡ አይችሉም ።" ሆኖም ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ በጥብቅ ፡ እንዲሠራበት ፡ የሚፈልጉ ፡ አገሮች ፡ እንኳ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ፍርድ ፡ ከፍተኛ ፡ ጠቃሚነት ፡ በመገንዘብ ፤ በተለይም ፡ የአገሩን ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ የሕግነት ፡ ዋጋ ፡ አያስጡትም ።[83] በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍጥር ፡ ፸፱ ፡ "ዳኞች ፡ የፍርድ ፡ ሥራን ፡ በሚሠሩበትም ፡ ጊዜ ፡ ከሕግ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ሥልጣን ፡ አይመሩም ፡" የሚለውን ፡ ካከበሩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ ሊያከናውን ፡ ይችላል ። እዚህ ፡

82 የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡) ገጽ ፡ ፩ ።

83 ፕላኒዮል ፡ ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ የተናገረውን ፡ ጂ ፡ ክሸቺኖቪች ፡ በ ፡ "ስታቱቶሪ ፡ ኢንተርፕሬቴሽን ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡" በ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፩ ፡ የተጠቀሰውን ፤ "ሕግ ፡ በሕይወቱ ፡ የሚገኝ ፡ በፍርዶች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡" የሚለውን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ተመልከት ።

ላይ ፡ ሕግ ፡ ሲባል ፡ በአዋጅ ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ በአዋጅ ፡ ለሚወጣ ፡ ሕግ ፡ ብልጫ ፡ ቢሰጥም (አዋጁን ፡ የሚያወጣው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሕዝቡን ፡ የወል ፡ ፈቃድ ፡ የያዘ ፡ የሕዝቡ ፡ እንደራሴ ፡ በመሆኑ ፡ ነው) ፡ ልማድ ፡ የዳኛ ፡ ፍርድ ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ሊጨመሩ ፡ ይገባል ። የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ነጻ ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራበት ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ያለመቃወስና ፡ ያለመጋጨት ፡ ሊደረጅ ፡ ይችላል ።

በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመኖች ፡ ሁሉ ፡ ከዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ ሕጎች ፡ ያለን ፡ ዕውቀት ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑ ፡ ያሳዝናል ።

ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ቀጥተኛ ፡ ምንጭ ፡ የለም ፤ ይህ ፡ ሁናቴ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ለክሶች ፡ ፍርድ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁናቴ ፡ አሳብ ፡ ለማግኘት ፡ የአገር ፡ ጎብኚዎችን ፡ ጽሑፍ ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። በታሪከ ፡ ነገሥት (ክሮኒክል) ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ፍርዶች ፡ ተጠቅሰውባቸው ፡ ብናገኝም (አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ፍርድ) ፡ ለምሳሌ ፡ ለጣዖት ፡ በመስገዳቸው ፡ ወንድ ፡ ልጁንና ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ በሞት ፡ እንዲቀጡ ፡ የፈረደባቸው ፡ የታወቀው ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ፍርድ ፡[84] ስለ ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ አናገኝባቸውም ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ያለን ፡ ምንጭ ፡ አገር ፡ ጎብኚዎች ፡ አንዳንድ ፡ ስለአዩዋቸው ፡ ሙግቶች ፡ የጻፉዋቸው ፡ መግለጫዎች ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ዐይነት ፡ የተጻፉት ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። በአልቫሬዝ ፡ መጽሐፍ ፡ አንዳንድ ፡ ፍርዶች ፡ ተጽፈው ፡ ይገኛሉ ፤ (በፖርቱጋሎች ፡ ላይ ፡ በጠብ ፡ የተነሳ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሱ ፡ እስላሞች ፡ አንዱ ፡ በገንዘብ ፡ የተቀጣ ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ በንጉሡ ፡ በሞት ፡ የተቀጣ ፡ ተጠቅሰዋል ፤ ከንጉሡ ፡ ፍርድ ፡ በመመንኮስ ፡ ለማምለጥ ፡ የሚሞክሩ ፡ በግርፋት ፡ ይቀጣሉ ፤)[85] ለፌብር ፡ የተባለው ፡ ጎብኚ ፡ በ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በጻፈው ፡ አብሮት ፡ የነበረ ፡ መንገደኛ ፡ ወፍ ፡ ለመግደል ፡ ወደ ፡ ዛፍ ፡ ሲተኩስ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ባቆሰለ ፡ ጊዜ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍል ፡ ተፈርዶበታል ።[86] መንገደኞች ፡ የጻፉዋቸው ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበረውን ፡ የፍርድ ፡ ሕግ ፡ አሟልተው ፡ ሊያቀርቡልን ፡ እንደማይችሉ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

በሁለተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻና ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ከዳኞች ፡ ፍርድ ፡ የተገኘው ፡ ሕግ ፡ በተሻለ ፡ ሁናቴ ፡ ሊገኝ ፡ የቻለው ፤ ይኸውም ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ከ፲፱፻፶ ፡ ዓ.ም. በኋላ ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ በመታተሙ ፡ ነው ። ጽሑፉ ፡ ስም ፡ ስላልተሰጠው ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ሕግ ፡ ዳይጀስት ፡</u> እንለዋለን ።[87]

ይህ ፡ ዳይጀስት (ከረጅሙ ፡ ባጭሩ ፡ የተጻፈ) ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚቴ ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ.ም. ገደማ ፡

84 ለዚህ ፡ ጂ ፡ ኮሩቮ ፡ <u>ሌ ፡ ክሮኒክ ፡ ደ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ በእደ ፡ ማርያም</u> ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፰፻፺፫ ፡) ከገጽ ፡ ፺፰ ፡ እስከ ፡ ፺፱ ፡ ተመልከት ።

85 እላይ ፡ በ፹፭ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ አልቫሬዝ ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ከገጽ ፡ ፫፻፹፫ ፡ እስከ ፡ ፫፻፹፬ ፡ እንዲሁም ፡ ከገጽ ፡ ፬፻፵፩ ፡ እስከ ፡ ፬፻፵፭ ፡ ተመልከት ።

86 ቲ ፡ ሌፌብር ፡ <u>ቦያዥ ፡ ኤን ፡ አቢሲኒ</u> ፡ በ፯ ፡ ቮሊዩም ፡ ፓሪስ ፡ (ቀን ፡ የለውም ፡) ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፶፱ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷፩ ፡ ተመልከት ።

87 ፳ ፡ ቮሊዩም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፫ ።

ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ትእዛዝ ፡ ሥራው ፡ ተጀመረ ። ሥራው ፡ የተዘጋጀው ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስትሩ ፡ በጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ስር ፡ በሚሠሩ ፡ አራት ፡ የኮሚቴ ፡ አባሎች ፤ እነሱም ፡ ብላታ ፡ ወልደ ፡ ኪሮስ ፡ የሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ምክትል ፡ ገዥ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደሳለኝ ፡ ቸርነት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ የሚመራመሩ ፡ ሊቅና ፡ አቶ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ደምሴ ፡ የቀድሞ ፡ ሬጅስትራር ፡ ናቸው ። ኮሚቴው ፡ የጥንተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ መጽሐፎች ፡ በተባሉት ፡ ከተመዘገቡት ፡ ቀድሞ ፡ ከተወሰኑ ፡ ፍርዶች ፡ ውስጥ ፡ በወንበሮች ፡ ወይም ፡ በንጉሡ ፡ ዳኞች ፡ ተፈርደው ፡ በአፈ ፡ ንጉሥ ፡ የጸደቁትን ፡ እየመረጠ ፡ በማጠናቀር ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሠራ ። በዚህ ፡ ሥራ ፡ ኮሚቴው ፡ ካልታወቀ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ፡ም፡ ከነበሩት ፡ ፍርዶች ፡ ውስጥ ፡ ከሰባት ፡ ሺ ፡ የሚበልጡ ፡ ፍርዶች ፡ በአምስት ፡ ትልልቅ ፡ መጽሐፎች ፡ ተጠቃልለው ፡ እንዲወጡ ፡ ኦ ድርጓል ። እነዚህ ፡ ፍርዶች ፡ የተገለበጡ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ ከሚሆኑ ፡ የጥንት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ መጽሐፎች ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሃያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ የተፈረዱ ፡ አንዳንድ ፡ ፍርዶች ፡ አይታጡበትም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ምናልባትም ፡ ፍርዶቹ ፡ መመዝገብ ፡ የጀመሩ ፡ በ ፲፱፻፳ ፡ ዓ.ም. ዓጼ ፡ ምኒልክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ሳያቋርጥ ፡ እየተመዘገበ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ባዘዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።[88] የፍርድ ፡ ቅጂዎቹ ፡ በሥርዐት ፡ ተመድበው ፡ በሁለት ፡ ትልልቅ ፡ ክፍል ፡ ተከፍለዋል ፤ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ ሦስት ፡ መጽሐፎች ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ የመጨረሻዎቹን ፡ ሁለት ፡ መጽሐፎች ፡ የያዘ ፡ ነው ። በሁለቱም ፡ ክፍሎች ፡ የተከተሉት ፡ ሥርዐት ፡ ያው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛው ፡ ለመጀመሪያው ፡ ማሟያ ፡ ነው ፡ ካልተባለ ፡ በቀር ፡ በሁለት ፡ የተከፈለበት ፡ ምክንያት ፡ አይታወቅም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዳይጀስቱ ፡ የተሰበሰበው ፡ በሁለተኛውና ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ስለሚገኙት ፡ ፍርዶች ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

ዳይጀስቱ ፡ ለነዚህ ፡ ዘመናት ፡ ጠቃሚ ፡ ምንጭ ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ የዳይጀስቱ ፡ ምንጮች ፡ የጥንተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ መጽሐፎች ፡ ደግሞ ፡ በአፈ ፡ ንጉሥ ፡ ያልጸደቁ ፡ ብዙ ፡ ፍርዶችም ፡ ስለሚገኙባቸው ፡ በይበልጥ ፡ ጠቃሚዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ መጽሐፎች ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ ይሆናሉ ፡ የተባለው ፡ ስለነዚሁ ፡ መጽሐፎች ፡ በዳይጀስቱ ፡ ከተሰጠው ፡ መምሪያ ፡ የተደረገ ፡ ግምት ፡ ነው ፤ መጽሐፎቹ ፡ በግምቱም ፡ ከተሰጠው ፡ ይበዙ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሊቃውንት ፡ ሊያገኙዋቸው ፡ አልቻሉም ።

በሁለተኛውና ፡ በሦስተኛው ፡ ዘመናት ፡ ከዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ስለሚገኘው ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ ምንጭ ፡ ደግሞ ፡ ከሃያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ የተፈረዱት ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዶች ፡ ናቸው ። ከአሁን ፡ በፊት ፡ እንደተገለጠው ፡ የቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ.ም. በኢትዮጵያ ፡ የተቋቋሙ ፡ በክፍለ ፡ አገሩ ፡ ንጉሦችና ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ከተደረጉት ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ የኢንተርናሽናል ፡

[88] ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ በ፳፪ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ቮሊዩም ፡ ፪ ፡ ከገጽ ፡ ፩፻፴፭ ፡ እስከ ፡ ፩፻፴፪ ፡ ተመልከት ።

ውሎች ፡ በአንዱ ፡ ነው ። ሆኖም ፤ የውሉ ፡ አንቀጽ ፡ ዓላማ ፡ በይበልጥ ፡ የታወቀው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በርዋን ፡ ከፍታ ፡ ከውጭ ፡ ያላት ፡ ግንኙነት (ወይም ፡ የውጭ ፡ ኃይል) ፡ እየተስፋፋ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጠቀሰው ፡ ያለ ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ ሰው ፡ ስለሚመለከት ፡ ማናቸውም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ ለቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ለፈረንሳይም ፡ በመስጠት ፡ ተደገመ ። ይኸውም ፡ የተሰጠው ፡ ስምምነቱን ፡ ባደረገው ፡ በፈረንሳይ ፡ እንደራሴ ፡ ስም ፡ የኮቡኮስኪ ፡ ውል ፡ እየተባለ ፡ በሚጠራው ፤ በ፲፱፻፰ ፡ ዓ.ም.በፈረንሳይና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውል ፡ በአንቀጽ ፡ ፯ ፡ ነው ። የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ አያያዝ (መብት) ፡ ይገባቸዋል ፡ በማለት ፤ በኢትዮጵያ ፡ ስለሚገኙ ፡ ዜጎቻቸው ፡ ሌሎችም ፡ መንግሥታት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ ። እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ውል ፡ አንቀጽ ፡ ቃሉ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

> "የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ አውሮፓውያን ፡ ሕግ ፡ እስከ ፡ ሆነ ፡ ድረስ ፡ ከአሁን ፡ ወዲያ ፡ በፈረንሳይ ፡ ዜጎች ፡ ወይም ፡ ጥገኞች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ በዐይነቱ ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ የወንጀልም ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ በፈረንሳይ ፡ ዳኝነት ፡ ስር ፡ ይሆናል ።
>
> በፈረንሳይ ፡ ዜጎች ፡ ወይም ፡ በጥገኞችና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዜጎች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ በዐይነቱ ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ የወንጀልም ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ በአንድ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ በሚያስችልና ፡ ከፈረንሳይ ፡ ቆንሲል ፡ ወይም ፡ ከወኪሉ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ በሚፈርድ ፡ ከአንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ይቀርባል ።
>
> ተከሳሹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ይዳኛል ።
>
> ተከሳሹ ፡ የፈረንሳይ ፡ ዜጋ ፡ ወይም ፡ ጥገኛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ይዳኛል ።
>
> ዳኞቹ ፡ በፍርዱ ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደሆነ ፡ በግርማዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ችሎት ፡ ይወሰናል" ። [89]

የውሉ ፡ ቃል ፡ ተከሳሹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ልዩው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚፈርድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ ይህ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ጥናት ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ሆኖም ፤ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወሰኑት ፡ የአንዳንድ ፡ ፍርዶች ፡ ትክክለኛነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የጠበቀ ፡ ክርክር ፡ ስላስነሳ ፡ እነዚህ ፡ ፍርዶች ፡ እንደ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ ሲጠኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት (ወይም ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት) ፡ በጣም ፡ ይሠራ ፡ የነበረውና ፡ አዘውትሮ ፡ የሚቀመጠው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ነበር (ይበልጡንም ፡ የእንግሊዝ ፡ ቆንስላ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት) ፤ በተለይ ፡ ከ፲፱፻፴ ፡ ዓ.ም.ጀምሮ ፡ የተፈረዱት ፡ የሚያብራሩ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። [90]በተጨማሪ ፡ የዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ተጽፎ ፡

89 ፒሲ ፡ በ፳፩ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በገጽ ፡ ፪፻፰ ፡ ተመልከት ።

90 ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ማርጀሪ ፡ ፔራም ፡ በ ፡ ዘ ፡ ገቨርንሜንት ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮፒያ ፡ ያለችውን ፡ (ለንደን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡) ገጽ ፡ ፪፻፩ ፡ ተመልከት ።

በአማርኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፡ የወጣው ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። [91]የሚያሳዝነው ፡ የቆንስላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አርሺቭ ፡ የት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አለመታወቁ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍርዶቹ ፡ ግልባጮች ፡ ከቆንስሎች ፡ ራፖር ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የተላኩ ፡ ስለሚመስል ፡ እንዲህ ፡ ያሉቱን ፡ ከፍርድ ፡ የተገኙ ፡ ሕጎች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ ማግኘት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። [92] እንዲሁም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ፍርዶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ ኤምባሲዎች ፡ ይገኙ ፡ ይሆናል ። [93]

ባለንበት ፡ ዘመን ፡ ስላለው ፡ ከፍርድ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ሕግ ፡ ብዙ ፡ አንናገርም ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ [94]ዓ.ም.አዲስ ፡ በተቋቋሙት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በየመደባቸው ፡ የፍርዱ ፡ ብዛት ፡ ሳያቋርጥ ፡ እየጨመረ ፡ ቢሄድም ፡ እነዚህን ፡ ፍርዶች ፡ ለማወቅ ፡ የሚቻለው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ እየሄዱ ፡ በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሆኖም ፤ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እየሄደ ፡ የፍርድ ፡ ቤትን ፡ መዝገብ ፡ መመልከት ፡ የማይችል ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በያመቱ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚፈረዱትን ፡ በሺ ፡ የሚቆጠሩትን ፡ ፍርዶች ፡ እየመረመረ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ የሚመርጥ ፡ በተለይ ፡ ተፈቅዶለት ፡ ነው ። [95]ሌሎች ፡ ፍርዶች ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከአፈ ፡ ንጉሡ ፡ አስፈቅዶ ፡ ያገኛቸው ፡ ናቸው ። ከነዚህ ፡ ፍርዶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተገኙት ፡ ጋር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ወጥተዋል ። [96]የመጽሔቱ ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሁሉ ፡ ያለውን ፡ የዳኞች ፡ ፍርድ ፡ የሚሰበስብ ፡ ቋሚ ፡ ድርጅት ፡ ሊኖር ፡ ወደሚችልበት ፡ መንገድ ፡ የሚወስድ ፡ የመጀመሪያ ፡ እርምጃ ፡ ነው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ፍርዶቹ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ታትመው ፡ ባያውቁ ፡ በመደምደሚያው ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ በፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ያለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ማውሳት ፡ ይገባል ። የአስተዳደርና ፡ የወታደር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ራፖርም ፡ ታትመው ፡ አያውቁም ። [97]

---

91 ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ዜርቮስ ፡ በ፳፰ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ ያለውን ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፳፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፳፯ ፡ ተመልከት ።

92 የኢትዮጵያ ፡ የቅልቅል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ በሚገኙባቸው ፡ በለንደን ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለው ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ሁናቴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናምናለን ።

93 በፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ አሁንም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በፈረንሳይ ፡ ኤምባሲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኙ ፡ ፍርዶችን ፡ ለመመልከት ፡ ችለናል ።

94 ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አዋጆች ፡ በ፶፩ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፶፩ ፡ እስከ ፡ ፻፲፩ ፡ ተመልከት ።

95 እነዚህ ፡ ፍርዶች ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ተቀምጠዋል ፤ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑት ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ታትመዋል ። ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ (ዋና ፡ የስታቲስቲክስ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡) የሚያሳትመውን ፡ የስታቲስቲክስ ፡ መግለጫ ፡ ተመልከት ።

96 ፲፰ ፡ ፍርዶች ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ሦስት ፡ መጽሔቶች ፡ ወጥተዋል ፡ ፱ ፡ ፍርዶች ፡ ደግሞ ፡ በሚቀጥለው ፡ ይወጣሉ ።

97 ይሁን ፡ እንጂ ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድና፡ በታክስ፡ ይግባኝ፡ ኮሚሲዮን፡ የተፈረዱ ፡ ፍርዶች ፡ በቅርቡ ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፡ በሚቀጥለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት፡ ይወጣሉ ።

## ፲ ፤ የሕግ ፡ ሳይንስ ።

የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ማለት ፡ በሥራ ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ በማጥናት (በመማር) ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸውና ፡ ሥራቸውንም ፡ ሕግን ፡ ለሕዝብ ፡ ማሳወቅ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ዘዴያቸውና ፡ እንዳቀራረባቸው ፡ ለሚኖሩበት ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ የሚገልጹት ፡ ሕግና ፡ የሕግ ፡ አቀራረብ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ አለመሆናቸው ፡ ሊታወቅ ፡ ይገባል ፤ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ሊቅነት ፡ የሚፈጽሙትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ሆነው ፡ ከሚሠሩት ፡ የተለየ ፡ ነው ።

የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሩቅ ፡ ከሆነው ፡ በመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመንም ፡ ይገኛል ። ያ ፡ የመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የታወቀውንና ፡ ለአራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ለአገሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተባለውን ፡ ሰጥትዋል ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እርግጠኛው ፡ የመጣበት ፡ ስፍራ ፡ ዛሬም ፡ ሊቃውንትን ፡ የሚያከራክር ፡ ነገር ፡ ነው ፤ በተለይም ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ምንጮች (ከዋናዎቹ ፡ አስቸጋሪ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ አንዱ ፡ ዓረብ ፡ ኖሞካኖን ፡ በተባለው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ቀጥተኛ ፡ ምንጭ ፡ የቢዛንትን ፡ ሕግና ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ በየራሳቸው ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሚገኙበት ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፡ ነው ።)[98] ዓረብ ፡ ኖሞካኖን ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ግብጻዊ ፡ ክርስቲያን ፡ ካኖን (የዲሲፕሊን ፡ ሕግ) ፡ ጸሐፊ ፡ በዓረብኛ ፡ ከጻፈው ፡ በ፲፭ኛውና ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ አጋማሽ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተተረጐመ ። መጽሐፉ ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ መገኘቱን ፡ እናውቃለን ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ጀምሮ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የሕግ ፡ መሠረት ፡ ሆነላቸው ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በአዋጅ ፡ ወጥቶ ፡ ባያውቅ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሁሉ ፡ ተሠራበት ፤ በትምህርት ፡ ቤትም (ሕግ ፡ በሚሰጥበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት) ፡ መማሪያ ፡ ሆነ ፤[99] በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በሰፊው ፡ ተተችትዋል (ተብራርቷል) ፤ ከግዕዝም ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ተተርጉሟል ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከትርጉሞቹ ፡ አንዱም ፡ አልታተመ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አማርኛው ፡ ከንግብራሪያው ፡ እንዲታተም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በቅርቡ ፡ ፈቅደዋል ።[100] ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በኢ ፡ ጉይዲ ፡ ወደ ፡ ጣሊያንኛ ፡ ተተርጉሞ ፡ ታትሞአል ፤[101] የእንግሊዝኛ ፡ ትርጉም ፡ ደግሞ ፡ በአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ፃድዋ ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያሳትመዋል ።[102] እዚህ ፡ ላይ ፡ የሥጋዊ ፡ ጉዳዮችን ፡

---

98 ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ደግሞ ፡ ናሊኖ ፡ ኮስታንዞ ፡ ቸሩሊና ፡ ኤሚሊያ ፡ ያወጥዋቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ በ፲፮ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በመጻሕፍቱ ፡ ዝርዝር ፡ የተሰጠውን ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ (መጀመሪያ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

99 ማስረጃው ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ አለንበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የሕግ ፡ ማስተማር ፡ ጉዳይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያሳያል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አገር ፡ ጎብኝዎችን ፡ ማመን ፡ ከተቻለ ፡ አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ማስተማሪያ ፡ ስፍራዎች ፡ የነበሩ ፡ ይመስላል ፤ (ለምሳሌ ፡ በ፳፮ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ለፌብር ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፻፳፰ ፡ ተመልከት) ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ትምህርቶች ፡ ዓላማቸው ፡ ቅስና ፡ ከሆኑት ፡ ትምህርቶች ፡ ጨርሰው ፡ አይለዩም ።

100 በ፲፱፻፳፩ ፡ መጨረሻ ፡ ወይም ፡ በ፲፱፻፳፪ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ሊታተም ፡ ነው ።

101 ኢ ፡ ጉይዲ ፡ ኢል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አ ፡ ሌጂስላሲዎኔ ፡ ዴይ ፡ ሬ ፡ ኮዲቼ ፡ ኤክሌዚያስቲኮ ፡ ኤ ፡ ቺቪሌ ፡ ዲ ፡ አቢሲኒያ ፡ በ፱ ፡ ቮሊዩም ፡ (ሮም ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፱) ።

የሚመለከተው ፡ ክፍል ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ መሆኑን ፡ ማስገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ፤ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ መንፈሣዊ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

ከመጀመሪያው ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ከሱ ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ወይም ፡ ከሱ ፡ ጥገኛነት ፡ ውጭ ፡ እንዳያድግ ፡ ነ ድርጓል ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ከውጭ ፡ መፈለግ ፡ ያሻል ። በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ አገሪቱ ፡ ሕግ ፡ የተጻፈ ፡ ከውጭ ፡ የተገኘ ፡ መግለጫ ፡ ሎውስ ፡ አንድ ፡ ኢንስቲቱሽንስ ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ኪንግዶም (የንጉሡ ፡ ግዛት ፡ ሕጎችና ፡ ድርጅቶች) ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በአንድ ፡ ባልታወቀ ፡ ሰው ፡ ለጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የተዘጋጀለት ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ጽሑፉ ፡ ብዙ ፡ የሚታወቅ ፡ ነገር ፡ የለም ። ይህ ፡ ያልታተመ ፡ ጽሑፍ ፡ ከብሩስ ፡ ሌሎች ፡ ሰነዶች ፡ ጋር ፡ አክስፎርድ ፡ በቦልዲያን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛል ።[103]

በመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ ሕግ ፡ የጻፉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ይመስላሉ ። እርግጥ ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ የመንገደኞች (አገር ፡ ጎብኝዎች) ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ጉዳዮች ፡ መግለጫ ፡ ይሰጣሉ ፤ ሆኖም ፤ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ አንዳቸውም ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም ።[104]

በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ገደማ ፡ የተደረጉ ፡ ጥናቶች ፡ አብዛኞቹ ፡ ሃይማኖትና ፡ ታሪክ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ አሉ ፤ ከነዚህም ፡ ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ አዋጅ ፡ ዲልማን ፡ የጻፈው ፤ ፔል ፡ ፕላት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዲደስቃሊያ (ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ ምንጭ) ፡ የጻፈው ፡ ናቸው ።[105]

ሁለተኛውን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ ስንመለከተው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ለውጥ ፡ ደርሰዋል ። ሆኖም ፤ ልንረዳው ፡ እንደቻል ነው (እንደተለመደው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ ማስተማርና ፡ ማተት ፡ መቀጠሉ ፡ ቢታመንም) ፡ በዚህ ፡ የአገሩን ፡ ሕግ ፡ ለማሳወቅ ፡ በተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አሁንም ፡ ተካፋይ ፡ አልሆኑም ። ሥራው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ ሥራውን ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ የሞከሩት ።

አንደኛ ፡ ነገር ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጥናት ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ፤ ይህም ፡ የተነሳሳው ፡ በ፲፰፻፺፯ ፡ ዓ.ም. እና ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ኢኛዚዎ ፡ ጉይዲ ፡ ድንቅ ፡ አድርጎ ፡ በሠራው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ትርጉም ፡ ነው ።[106]

---

102 በ፲፱፻፷፰ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ ሊታተም ፡ ነው ። ይህ ፡ ትርጉም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እንደሚመለከት ፡ ለመላው ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ።

103 በቦድሌያን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የብሩስን ፡ ጽሑፎች፡ ቍጥር፡ ፹፰ ፡ እና፡ ፺፪ ፡ ተመልከት ። የነዚህ ፡ ሁለት ፡ ጽሑፎች ፡ ማይክሮ ፡ ፊልም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ተቀምጥዋል ።

104 የኢልባሬዝንና ፡ የሊፌብርን ፡ ጽሑፎች ፡ (ጥቂቶቹን ፡ ብቻ ፡ ለማውሳት ፡) በ፷፩ኛውና ፡ በ፹፩ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ ተመልከት ።

105 በ፲፮ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በመጽሐፎች ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል፡ (መጀመሪያ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

106 በ፺፩ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ እላይ ፡ ተመልከት ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ይልቅ ፡ ሊቃውንቱ (አብዛኞቹ ፡ ጣሊያኖች) ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚጽፉ ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ ነበር ፤ በተለይም ፡ ስለ ፡ ኤርትራ ፡ ልማድ ፡ ሕግ ፡ በዘመኑ ፡ የተዘጋጀውን ፡ የኮንቲ ፡ ሮሲኒን ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ አንስተነዋል ። [107] ሳይነገር ፡ ሊታለፍ ፡ የማይገባው ፡ ደግሞ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ እነዚህ ፡ ጥናቶች ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በልማድ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ብንመድባቸው ፡ በውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ደንበኛው ፡ ክፍላቸው ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ነው ።

ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሁናቴዎች ፡ የተደረጉ ፡ ሌሎች ፡ ጥናቶችም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ታትመዋል ፤ እነሱም ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ዶኩማዎች ፡ የተደረጉ ፡ ጥናቶች ፡ ሲሆኑ ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ የዶኩማዎቹን ፡ የመጀመሪያ ፡ እትም ፡ ይዘው ፡ እናገኛለን ። [108]

ሦስተኛው ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ በኩል ፡ ከሁለተኛው ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የተለዬ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ። ምናልባት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፡ እየበዛ ፡ ሄዶ ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ጥናቶች ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ አሳይተዋል ፡ ለማለት ፡ ገና ፡ አልተቻለም ። በዚህም ፡ ዘመን ፡ በቀድሞው ፡ ዘመን ፡ ዐይነት ፡ ጥናቶች ፡ መታተማቸውን ፡ አላቋረጡም ፤ ጎልቶ ፡ የሚታየው ፡ ለውጥ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በታወጀው ፡ በአንዳንድ ፡ ሕግ ፡ የሊቃውንቱ ፡ መሳብ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፤ ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ አንዳንድ ፡ ደንበኛና ፡ እውነተኛ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ጥናቶች ፡ ተጀመሩ ። [109]

የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ በደንብ ፡ የተጀመረው ፡ በመጨረሻው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነው ።

አንደኛ ፡ ከሁለተኛ ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ አቋም ፡ በጠቅላላው ፡ የሚገልጹ ፡ መጽሐፎች ፡ ታተሙ ። ከታተሙትም ፡ መጽሐፎች ፡ እንደ ፡ ደራሲዎቹ ፡ ጠባይ ፡ ልዩነትና ፡ እንደ ፡ አቀራረባቸው ፡ ልዩነት ፡ ጨርሰው ፡ የማይመሳሰሉ ፤ የማርዠሪ ፡ ፔራም ፡ ዘ ፡ ገቨርንሜንት ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት) ፡ [110] እና ፡ የናታን ፡ ማሬይን ፡ ዘ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ኤምፓየር ፡ ፌዴሬሽን ፡ አንድ ፡ ሎውስ (የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ፌዴሬሽንና ፡ ሕጎች) ፡ [111] የተባሉት ፡ ሁለት ፡ መጽሐፎች ፡ ናቸው ። ስለዘመኑ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ከነዚህ ፡ ሌላ ፡ አጫጭር ፡ ጽሑፎችም ፡ ተጽፈዋል ። [112]

---

107 በ፳፪ኛውና ፡ በ፳፫ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ እላይ ፡ ተመልከት ።

108 በመጽሐፎች ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ (ሁለተኛ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

109 ያንኑ ፡ ግን ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ።

110 ለንደን ፡ (፲፱፻፵፰) ።

111 ሮተርዳም ፡ (፲፱፻፶፭) ፤ ይህ ፡ እትም ፡ ደራሲው ፡ የጻፉቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አርእስቶች ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ በመመደብ ፡ አንድ ፡ የእጅ ፡ እትም ፡ አስቀድሞ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ፤ የመጽሐፉም ፡ ስም ፡ ሀንድቡክ ፡ ቱ ፡ ዘ ፡ ሎስ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፱) ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጁዲሻል ፡ ሲስተም ፡ አንድ ፡ ዘ ፡ ሎስ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሚል ፡ ስያሜ ፡ የመጀመሪያው ፡ እትም ፡ በ፲፱፻፶፩ ፡ ወጣ ።

112 የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ (በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመንና ፡ ከ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ.ም. በፊት ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ባለምበራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ በ፲፱፻፱ ፡ ዓ.ም. ዝክረ ፡ ነገርን ፡ በማሳተም ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አበርክተዋል ። መጽሐፉ ፡ ከ፲፱፻፳ ፡ ዓ.ም. (የመጀመሪያዎቹ ፡ ሚኒስትሮች ፡ የተሾሙበት) ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ.ም. (ጦርነቱ ፡ እስከ ፡ ተጀመረበት) ፡ ባሉት ፡ በነዚያ ፡ ከፍተኛ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በመጽሐፉ ፡ የታተሙትን ፡ ዶኩማዎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለነዚሁ ፡ ዶኩማዎች ፡ ሰፊ ፡ መግለጫ (ሀተታ) ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ በአማርኛ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የታተመው ፡ በብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ አልታወቀም ። [113]

በመጨረሻም ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ ከፍተኛ ፡ የእድገት ፡ እርምጃ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎቱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ለማደርጀትና ፡ ለማስራጨት ፡ የሆነው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡ ነው ። ይህን፡ ለመረዳት ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በተቋቋመ ፡ በዚህ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ራሱ ፡ ያሳተማቸውንና ፡ በዋስትናው (በእርዳታው) ፡ የታተሙትን ፡ ጽሑፎች ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ። <u>ከየኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ቋሚ ፡ ነገሮችም ፡ መጻሕፍት ፡ ታትመዋል ። [114] ይህንና ፡ በያመቱ ፡ የሚመረቁትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ ሊቆች ፡ ስንመለከት ፡ የአገሩ ፡ የወደፊት ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ዕድል ፡ በደህና ፡ እጅ ፡ ገብትዋል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ጉልህ ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ምልክቶች ፡ እርግጠኛውን ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ አብዛኛው ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ገና ፡ ያልታወቀ ፡ መሆኑን ፡ ሊሰውሩት ፡ አይገባም ። በልማድ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ እንደ ተጠቀሰው ፡ [115] ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን (አንዳንዶቹ ፡ በመንግሥቱ ፡ አስተዳደር ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ያሉ) ፡ ጠቃሚ ፡ የሕግ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ለተተኪዎቻቸው ፡ ማስተማሪያ ፡ ጽፈዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ለአንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉ ፡ ጽሑፎች ፡ አልታተሙም ፤ ሊመለከትዋቸው ፡ የሚፈልጉም ፡ ሰዎች ፡ ሊያገኙዋቸው ፡ አይችሉም ። በውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ የነዚህ ፡ ጽሑፎች ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ መውጫቸው (መገለጫቸው) ፡ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ደራሲዎቻቸው ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ተረድተው ፡ ሊቃውንት ፡ እንዲያገኙዋቸው ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚፈቅዱ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

በመጨረሻም ፡ ልናነሳው ፡ የሚገባ ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ጥናት ፡ ሊያበረክት ፡ የሚችልበት ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ በአገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ቦታ ፡ የሚሠራበት ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይህም ፡ ከ፲፩ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መነሻ ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከእስላም ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ ከነበራት ፡ ትግል ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በከፊል ፡ የእስላምን ፡ ሕግ ፡ ተቀብሎ ፡ ዛሬም ፡ ይሠራበታል ። ዛሬ ፡ በአገሩ ፡ ሦስት ፡ ዐይነት ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች (እነሱም ፡ ሻፊት ፡ መለከት ፡ እና ፡ ሐናፊት) ፡ የሚከተሉ ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ባሉበት ፡

---

[113] በ፰፪ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ ተመልከት ፤ የጽሑፉን ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተርጉመዋቸዋል ።

[114] ፐብሊኬሽንስ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፋከልቲ ፡ ኦፍ ፡ ሎ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፈርስት ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ ስር ፡ የተመደቡትን ፡ በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ (በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

[115] እላይ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ተመልከት ።

ሁሉ ፡ በአካባቢው ፡ ስፍራ ፡ ከሚገኘው ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ይኖራሉ ፡ ወይም ፡ ከልማዱ ፡ ይጋጫሉ ። ከአንዳንድ ፡ በአጠቃላይ ፡ ሁናቴ ፡ ከተጻፉ ፡ መጽሐፎች ፡ በቀር ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሚሠራበት ፡ ሁናቴ ፡ የሚገልጹ ፡ ምንጮች ፡ እምብዛም ፡ አይገኙ ፤ ስለዚህ ፡ ምንጮቹ ፡ በአንዳንድ ፡ ዶኩማዎች ፡ የታሪክ ፡ ወይም ፡ የሳይንስ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ አልፈው ፡ አልፈው ፡ የተነገሩት ፡ ናቸው ። [116]

የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ በጨቅላነቱ ፡ ያለ ፡ ይመስላል ፤ ስለዚህ ፡ ስለ ፡ አገሪቱ ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ ተቆርቋሪ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ እንዲያድግ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

፭ ፤ የሕግ ፡ ሰነዶች (ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ ዶኩማዎች) ።

የሕግ ፡ ሰነዶች ፡ ማለት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው (በዕለት ፡ ኑሮው) ፡ የዕለት ፡ ተግባሩን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ ውጤት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚያዘጋጃቸው ፡ ማናቸውም ፡ ጽሑፎች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ምንጫቸው ፡ የግልና ፡ የሕዝብ ፡ በመባል ፡ ሊመደቡ ፡ ይችላሉ ፤ የመጀመሪያዎቹ ፡ ከግል ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆኑ ፡ ሁለተኛዎቹ ፡ ደግሞ ፡ ከመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ሥራ ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ።

የግል ፡ ሰነዶች ፡ በሕግ ፡ ምንጭነት ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ለማድረግ ፡ ዋናው ፡ ችግር ፡ አንደኛ ፡ ሰነዶቹ ፡ ታትመው ፡ አያውቁም ፤ ሁለተኛ ፡ ሰነዶቹ ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ አይጠቅሙንም ፡ ሲሉ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ያጠፉዋቸዋል (ይቀድድዋቸዋል) ። ደግነቱ ፡ ከነዚህ ፡ የግል ፡ ሰነዶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ የማያቋርጥ (ዘለዓለማዊ) ፡ የሆነ ፡ መብት ፡ ስለሚያቋቁሙ ፡ ለብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ተጠብቀው ፡ ይገኛሉ ። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ የሕግን ፡ ጉዳይ ፡ በማይመለከቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግበው ፡ ይገኛሉ ፤ (ለምሳሌ ፡ በገዳማት ፡ በሚገኙ ፡ የሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ) ፡ እነዚህም ፡ ጽሑፎች ፤ (የሃይማኖት ፡ መጽሐፎች) ፡ ተጠብቀው ፡ ስለሚኖሩ ፡ ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ሰነዶችም ፡ አብረው ፡ ይገኛሉ ። [117]

---

[116] በይበልጥ ፡ ጆ ፡ ኤስ ፡ ትሪሚንግሀም ፡ ኢስላም ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ለንዶን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡) ተመልከት ። እንዲሁም ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ እስላም ፡ ስላለው ፡ መጫን ፡ በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል (በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) ተመልከት ።

[117] እነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ አብዛኞቹ ፡ የሌሎች ፡ የታሪክ ፡ ሰነዶች ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ በመሆን ፡ ይገኛሉ ፤ በሙዚየም ፡ ወይም ፡ በቤተመዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ካታሎግ ፡ እየተመለከተ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሰነዶች ፡ እየመረመረ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ጉዳይ ፡ የተጻፉትን ፡ ከውስጣቸው ፡ ማውጣት ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ ተግባር ፡ ነው ። በመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ሰነዶች ፡ ክፍል ፡ (በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡) በውጭ ፡ አገር ፡ ሙዚየም ፡ ወይም ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ከሚገኙ ፡ ዋናዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰነዶች ፡ ካታሎግ ፡ ተመልከት ። በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አርኪዎሎጂ ፡ ኢንስቲቱት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚገኙ ፡ ከነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ የአንዳንዶቹን ፡ ፎቶ ፡ ኮፒ ፡ በቅርቡ ፡ ወስድዋል ።

በሁለተኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ የሕግ ፡ ጉዳይ ፡ የያዘ ፡ የግል ፡ ሰነዶችን ፡ ማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ሕዝብ ፡ እንዲያውቃቸው ፡ በጋዜጣ ፡ ከወጡ ፡ ከአንዳንድ ፡ ሰነዶች (ለምሳሌ ፤ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ውርስና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ጉዳይ ፡ የሚወጡ ፡ ማስታወቂያዎች) ፡ በቀር ፡ የግል ፡ ሰነዶች ፡ ስለሚቀጥሉትም ፡ ዘመናት ፡ ማግኘት ፡ አይቻልም ።[118] ተስፋ ፡ የምናደርግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እንዲታወቅ ፡ ለማድረግ ፡ የሚወዱ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አይጠቀሙንም ፡ የሚሏቸውን ፡ የግል ፡ ሰነዶች ፡ እንደ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ባሉት ፡ ስፍራዎች ፡ ለማኖር ፡ ይፈቅዳሉ ፡ ብለን ፡ ነው ።

የሕዝብ ፡ ሰነዶች ፡ የሆኑ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ብዙዎቹ ፡ የመንግሥትን ፡ ራፖርና ፡ ኮሬስፖንዳንስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲሆኑ ፤ እንደዚህ ፡ ያሉቱን ፡ ከዐይነታቸው ፡ የተነሳ ፡ ሕዝብና ፡ ሊቃውንት ፡ ሊያገኙዋቸው ፡ አይችሉም ። ይህ ፡ ተፈጻሚ ፡ የማይሆነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ያሏትን ፡ ጉዳዮች ፡ በሚመለከቱ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ በሚገኙ ፡ ሰነዶች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የአምሳ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ካለፋቸው ፡ በኋላ ፡ እነዚህን ፡ ሰነዶች ፡ ማየት ፡ ይቻላል ፤ ለምሳሌ ፤ በለንደን ፡ የሚገኘው ፡ የሕዝብ ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ ከ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ.ም. በፊት ፡ ያሉትን ፡ ሰነዶች ፡ ማየት ፡ ይፈቅዳል ። ለማየት ፡ በሚፈቀዱት ፡ ሰነዶች ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያውንና ፡ የሁለተኛውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ ክፍለ ፡ ዘመኖች ፡ የሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ የሕዝብ ፡ ሰነዶች ፡ ልናገኝበት ፡ እንችላለን ።[119] በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ድርጅት ፡ ባለመኖሩ ፡ ሰነዶችን ፡ ማግኘት ፡ በፍጹም ፡ አይቻልም ።

### ለ) ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ያሉ ፡ ምንጮች ።

የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ በደንብ ፡ ለማጥናት ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ያሉ ፡ ጽሑፎች ፡ ስላላቸው ፡ ስፍራ ፡ ብዙ ፡ እንናገርም ፤ ከአሁኑ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ ስንናገር ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ያልሆኑ ፡ ጽሑፎችም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እንዲታወቅ ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ የሚረዱ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸናል ። ከታሪክ ፡ ምንጮች ፡ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ካሉት ፤ ከጽሑፍ ፡ ምንጮች ፡ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ አገር ፡ ጎብኝዎች ፡ ራፖር ፡ ካሉት ፤ ከሃይማኖት ፡ ምንጮችም ፡ ሳይቀር ፡ ለምሳሌ ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጽሑፍ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ዘመን ፡ ስለሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃ ፡ ይገኛል ። ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ያሉ ፡ ምንጮች ፡ ለቅርቡ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ እንኳ ፡ ባይሆኑ ፡ ሊያገለግሉ ፡ ይችላሉ ፤ ከነዚህም ፡ ለምሳሌ ፡ በዚህ ፡ በሃያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የወጡት ፡ ጋዜጦች ፡ ናቸው ።

---

118 የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በደንብ ፡ መሰብሰብ ፡ ጀምሯል ።

119 የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጥናት ፡ አምና ፡ ተጀምሮ ፡ ነበር ፤ ዘንድሮም ፡ በአንድ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ጥናቱ ፡ በደንብ ፡ ይቀጥላል ።